ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 361 ጳጉሜን 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# አፍሪካ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሰሩ የምርምር ተቋማት ላይ ኢንቨስት ልታደርግ ይገባታል



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሠሩ የምርምር ተቋማት ላይ ኢንቨስት ልታደርግ እንደሚገባ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ።

በኬንያ ናይሮቢ በተካሄደው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባዔ ላይ ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፤ እንደ አፍሪካ አህጉር የምርምር ሥራዎች ላይ የአቅም ማጎልበቻ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

በመድረኩ ኢትዮጵያ ባለፉት 10 ዓመታት የአየር ንብረት ለውጥ በፈጠራቸው ቀውሶች ድርቅ፣ ጎርፍና የአንበጣ መንጋ ሚሊዮኖች ለጉዳት መዳረጋቸውን አንስተዋል።

በሌላ በኩል፣ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ ውስጥ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የመገንባትን ጉዳይ አካታ እየሰራች መሆኗን ገልፀዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር የመጀመሪያ ምዕራፍ ትግበራ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል እንደ ህዝብም የአረንጓዴ ልማት ማስረፅ ስለመቻሉ ጠቁመዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ ልክ እንደ ሰላምና መረጋጋት ሁሉ የአህጉሪቱ ዋነኛ አጀንዳ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፣ በተፈጥሮ ሀብት በበለፀገች አህጉር ውስጥ እየኖርን ለምን ደሃ ሆንን የሚለውን ለህዝባችን በተለይም ለወጣቱ ማስረዳት ከባድ ነው ብለዋል።

አፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዘጋጀችው በአየር ንብረት ላይ የሚመክር ጉባዔ ከውይይት መድረክነት ባለፈ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የሚጀመርበት ነው ብለዋል።

በግብርናው ዘርፍ በተለይም በበጋ ስንዴ ምርት የሀገር ወስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ጎን ለጎን ስንዴን ለውጭ ንግድ ማቅረብ ላይ የተሠራው ሥራ ትልቅ ዕመርታ የታየበት ስለመሆኑም አንስተዋል።

የዓባይ ግድብን ጨምሮ የኃይል አማራጮች ከብክለት ነፃ ለመጠቀም እየተደረገ ስላለው ጥረትም ገልጸዋል።











## አገልጋይነት

### ያለንን ጊዜና ዕውቀት ያለስስት የመስጠት ስብዕና መላበስ ይጠይቃል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- አገልጋይነት ያለንን ጊዜና እውቀት ያለስስት የመስጠት ስብእና መላበስን የሚጠይቅ፣ ወደ ኃላፊነት የሚመጣ ሰውም ለማገልገል የቆረጠ መሆን እንዳለበት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡

የአገልጋይነት ስሜትን በመላበስ ፈጣንና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያቀርቡ ማነሳሳትን ዓላማ ያደረገው "የአገልግሎት ቀን" በሀገር አቀፍ ደረጃ እየታሰበ ይገኛል፡፡

ከንቲባ አዳነች ከዘመን መጽሄት ጋር በነበራቸው


አገልጋይነት ያለንን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


## "አገልጋይነት በፈጣሪም ሆነ በሰዎች ዘንድ ዋጋ የሚያሰጥ ዕድል ነው"

- የጤና ሚኒስትር ሊያ ታደሰ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- አገልጋይነት በፈጣሪም ሆነ በሰዎች ዘንድ ዋጋ የሚያሰጥ ዕድል ነውና በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል ሲሉ የጤና ሚኒስትር ሊያ ታደሰ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡


ጳጉሜን አንድ የሚከበረውን የአገልጋይነት ቀን በማስመልከት "ኢትዮጵያን እናገልግል" በሚል መሪ ሃሳብ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በጤናው ዘርፍ ያለውን አገልግሎት በተመለከተ የመወያያ ጽሁፍ ያቀረቡት የጤና ሚኒስትር ሊያ ታደሰ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የጤና ባለሙያዎች ባልተመቹ ሁኔታዎች ኢትዮጵያና ዜጎቿን ለማገልገል የሚያደርጉት


"አገልጋይነት በፈጣሪም ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ






## ሆስፒታሉ በሚሰጠው አገልግሎት ህብረተሰቡን ደስተኛም፤ አጋዥም ማድረግ ችሏል


ገጽ 8











አቶ መልካሙ ጥሩነህ

# በመዲናዋ

## በነፃ የህክምና አገልግሎት ከ112 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እየሰጠ በሚገኘው የክረምት ነፃ የህክምና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ112 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታወቀ፡፡ ለነዋሪዎች በተደረገ ህክምና እስካሁን ከ28 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ብር ወጪ መደረጉም ተገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የህክምና አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ መልካሙ ጥሩነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ከሰኔ ወር ጀምሮ እየሰጠ በሚገኘው የክረምት ነፃ የቅድመ በሽታ የመከላከልና የህክምና አገልግሎት 112 ሺህ 624 ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል፡፡ ለነጻ ህክምናው እስካሁን ከ28 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ብር ወጪ ተደርጓል፡፡

በመዲናዋ «በጎነት ለጤናችን» በሚል መሪ ቃል የክረምት ነፃ የበጎ ፈቃድ የቅድመ በሽታ የመከላከልና ህክምና አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ አመልክተው፤ በዚህም መርሃ-ግብር ለ100 ሺህ ነዋሪዎችን አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት እስካሁን 112 ሺህ 624 ሰዎች ነጻ የህክምና አገልግሎት መስጠት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በመዲናዋ እየተሰጠ ባለው የክረምት ነፃ የቅድመ በሽታ የመከላከልና መደበኛ የህክምና አገልግሎት ሥራ ምርመራ ከተደረገላቸው 112 ሺህ 624 ሰዎች ውስጥ 64 ሺህ 826 አዋቂዎች፣ 27 ሺህ 807 የሚሆኑት ሕፃናት ሲሆኑ እናቶችና ወጣቶችም ይገኙበታል ተብሏል፡፡

በተጨማሪም ምርመራ ከተደረገላቸው 112 ሺህ 624 ሰዎች ውስጥ ሁለት ሺህ 713 የሚሆኑት የተገኙባቸው በሽታዎች መደበኛ ህክምና እና የባለሙያ ክትትል የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው ወደ ሆስፒታል ተልከው እየታከሙ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

በመርሃ ግብሩም 16 ሺህ 500 የጤና ባለሙያዎች እየተሳተፉ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ የደም ግፊትና ስኳር በሽታ ልየታ፣ የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ እና ከአንገት በላይ ህክምና ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባቸው የሚገኙ በሽታዎች ናቸው ብለዋል፡፡

በተቋሙ በክረምት ነፃ ቅድመ በሽታ የመከላከልና ህክምና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እየተሰጡ የሚገኙ የህክምናና የባለሙያ ምክሮችን በመደበኛ አገልግሎት ለመስጠትና አጠናክሮ ለማስቀጠል የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ ነው ሲሉ አመልክተዋል፡፡

# የግል ድርጅቶች የራሳቸውን የብድር ሰነድ ገበያ ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እና ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን የግል ድርጅቶች የራሳቸውን የብድር ሰነድ ገበያ ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል ስምምነት ተፈራረሙ።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ብሩክ ታዬ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ስምምነቱ በካፒታል ገበያ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ፣ ቴክኒካል ድጋፍ ለማግኘት እና የሙከራ ግብይት (ትራንዛክሽን) ለማድረግ የሚያስችል ነው። ይህም የልማት ድርጅቶችና የግል ተቋማት የራሳቸውን የብድር ሰነድ ገበያ ላይ ሸጠው ተጨማሪ ፋይናንስ እንዲያገኙ ያስችላል።

ከዚህ ቀደም መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ለሽያጭ የሚያወጣቸው ሰነዶች ቢኖሩም ሌሎች ትላልቅ የልማት ድርጅቶች የብድር ሰነድ ገበያ ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት የለም ያሉት ዶክተር ብሩክ፤ ስምምነቱ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ለማሳደግ የሚያስችል ነው። በ2016 በጀት ዓመት ካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ይጀመራል ብለዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው፤ የካፒታል ገበያ ባለሀብቶች፣ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች ወይም መንግሥት ለሚያስፈልጋቸው ኢንቨስትመንት ካፒታል በጥሬ ገንዘብ አሊያም በአይነት የሚያሰባስቡበትና የሚያገኙበት ገበያ ነው። ይህም ካፒታል በማሰባሰብ፣ የገንዘብ ሥርዓቱን በአዲዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ እና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት ያግዛል ብለዋል።

በቀላሉ ቢዝነስ ለመጀመር፣ ለማስፋፋት እና የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎችን በአፋጣኝ ለማግኘት እንዲሁም የውጭ ኢንቨስተሮችን በቀላሉ ለመሳብና ከትናንሽ ቢዝነሶች እስከ ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ለመመስረት እድል ይፈጥራል። በተለይም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሆነው በተለያዩ



የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሳተፉ ሰፊ እድል እንደሚፈጥር ነው የገለጹት።

በአፍሪካ የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን ዳይሬክተር ሚስተር አልዩ በማጊያ በበኩላቸው፤ የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ድርጅቶች የራሳቸውን የብድር ሰነድ ገበያ ላይ ማዋል እንዲችሉ የበኩሉን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልፀዋል።

ከዚህ ስምምነት በኋላም ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ጋር በርካታ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት እንደሚፈልጉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ ያስፈለገው ካፒታል በማሰባሰብ፣ የገንዘብ ሥርዓቱን በአዲዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት አሠራርን በማስፋፋት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት ለመደገፍ እንዲቻል መሆኑን አብራርተዋል።

በተጨማሪም በሀገሪቱ የፋይናንስ ሥርዓት ላይ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ስጋቶችን ለመለየት፣ ለመከላከልና ለመቀነስ በካፒታል ገበያ ላይ ጠንካራ የቅርብ ክትትልና የቅኝት ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ መሆኑን በባለሥልጣኑ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1248 /2013 ተደንግጓል።

# በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጭ ማዕቀፎች ዙሪያ ሲካሄድ የቆየው የሕዝብ ውይይት ተጠናቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የባለሙያዎች ቡድን በመላው የሀገሪቱ አካባቢዎች ሲካሄድ የነበረው የሕዝብ ውይይት መጠናቀቁን ይፋ ሆነ።

የባለሙያዎች ቡድን ሲያከናውናቸው የቆዩ ተግባራትን አስመልክቶ መግለጫ ሰጥቷል። በመግለጫውም በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊነት ታምኖበት ሁሉን አቀፍ አካታችና ተመጋጋቢ የሆነ ፖሊሲ ለማዘጋጀት ባለፉት ወራቶች የግብዓት ማሰባሰቢያ የውይይት መድረኮች ሲካሄድ መቆየቱ ተገልጿል።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ቡድን አስተባባሪ ታደሰ ካሳ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ብሔራዊ ሃሳብን የባለቤትነትን መንፈስ ባረጋገጠ መልኩ የተቃኘ መሆኑንና የሚቀርቡ ምርጫዎች ሁሉ እንደ ሀገር ህዝብ ተስፋ የሚያደርገው ጉዳይ ላይ ወሳኝነት አለው።

የምክክር ሂደቱም ቅድመ ፖሊሲ ከመቅረፅ ጀምሮ ሪፖርት መፃፍ፣ ረቂቅ ማሰናዳት እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቶና ሰነዱን አዘጋጅቶ መላክን እንደሚያካትት አብራርተዋል፡፡

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ዝግጅት በሀገራችን የህግና የፖሊሲ አወጣጥ ታሪክ ያልተለመደና አዲስ ነገርን ይዞ የመጣ ነው ያሉት አስተባባሪው፤ ከላይ ወደታች የነበረውን የፖሊሲ አወጣጥ በማስቀረት ከታች ወደላይ አሠራርን የተከተለና ለህዝቡ ሰፊ ዕድል



ታደሰ ካሳ (ዶ/ር)

የሰጠ ነው ብለዋል።

በዚህም በመንግሥት በኩል ሀገርና ህዝብ የሚፈልጉትን ነገር አንጥሮ ለመለየት ዕድል አካታችነት፣ ግልፀኝነት፣ ገለልተኝነትና ሌሎች መርሆዎችን በተሻለ መልኩ ለመተግበርም ያስቻለ መሆኑን አንስተዋል።

በእስካሁኑ ሂደትም በአዲስ አበባ፣ በ12 ክልሎችና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በጥቅሉ በ59 አካባቢዎች ውይይቶች መደረጋቸውንና ከ40 ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ከ200 በላይ የሕግ መምህራን በሂደቱ ተሳታፊ መሆናቸውን ገልፀዋል።

በመድረኮቹ የተሰበሰቡ ግብዓቶችን ማደራጀትና መተንተን፣ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ የማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀትና በመጨረሻም ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ አዘጋጅቶ ማስረከብ ቀጣይ የቡድኑ ተግባራት መሆናቸውንም አብራርተዋል።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከሀገራዊ ምክክር ጋር ያለውን ልዩነትና ተመጋጋቢነት ያብራሩት የቡድኑ አባል አቶ ምስጋናው ሙሉጌታ፤ ውስብስብና መጠነ ሰፊ ችግር ባለባቸው ሀገራት ከነዚህ አማራጮች በዘለለ ሌሎች ሂደቶችም በአንድ ላይ እንደሚተገበሩ አንስተዋል።

ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ ፖሊሲዎችም ተመጋጋቢ ነገር ግን የተለያየ አውድና ግብ ያላቸው ሂደቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ሁለቱም ለዘላቂ ሰላምና ለሀገረ መንግሥት ግንባታ የራሳቸው መሠረታዊ አስተዋፅኦ እንዳላቸው፤ የሽግግር ፍትህ ዋነኛው ትኩረት ተፈፀሙ የሚባሉ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ መሆኑን እና በእነዚህ ሂደቶች ክስ የሚኖር መሆኑን አመላክተዋል።

ከተቋማዊ አደረጃጀት አንፃርም፥ የሽግግር ፍትህ በሁለት ዓይነት እንደሚደራጅና እነዚህም የእውነት ኮሚሽንና ፍርድ ቤት መሆናቸውን፤ ሀገራዊ ምክክር በኮሚቴ መሰል ቡድኖች እንደሚደራጅና በጥቅሉ በሽግግር ፍትህ አማራጮች እንደ አንድ አማራጭ እንደሚካተት አብራርተዋል፡፡

በመጨረሻም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ባለሙያዎቹ ከጋዜጠኞች ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተው መግለጫው መጠናቀቁን ከፍትሕ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ተመላክቷል።



# “አቅም ያነሳቸው ዜጎች አዲሱን ዓመት በአዲስ ቤትና በአዲስ ተስፋ እንዲቀበሉ አድርገናል”

- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- አቅም ያነሳቸው ነዋሪዎች አዲሱን ዓመት በአዲስ ቤት፤ በአዲስ ተስፋ እንዲቀበሉ አድርገናል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የተገነቡ አንድ ሺህ 680 የመኖሪያ ቤቶችን አቅም ላነሳቸውና በችግር ውስጥ ለሚገኙ የሀገር ባለውለታዎች አስረክበዋል።

አቅም ላነሳቸው የከተማዋ ነዋሪዎችና ለሀገር ባለውለታዎች አዲሱን ዓመት በደስታና በተስፋ እንዲቀበሉ በማሰብ ቤቶችን ገንብተን አስረክበናል ሲሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቁልፍ ርክክቡ ወቅት ተናግረዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በመዲናዋ በአስከፊ ችግር ውስጥ ለሚገኙ የሀገር ባለውለታዎች፣ አቅም ላነሳቸው ዜጎች እንዲሁም ለአካል ጉዳተኛ ነዋሪዎች አስፈላጊ የመገልገያ ዕቃዎች የተሟሉላቸውን አንድ ሺህ 680 መኖሪያ ቤቶችን ማስረከቡንም አስታውቀዋል።

ከተባበርንና በጋራ ከሰራን አቅማችን ትልቅ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ የሚሰሩ ዕጆች ሁሉ ወደ ብልፅግና ስለሚያመሩን በጎ አገልግሎቶቻችንን እያጎለበትን መቀጠል ይኖርብናል ብለዋል።

የነዋሪውን የኑሮ ጫና ለማቃለል ቃል በገባነው መሠረት በሁሉም ዘርፍ ተባብረን እየሠራንና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረግን ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ከተማችን አደገች የምንለው የነዋሪዎቿ ሕይወት ሲቀየር በመሆኑ ያለንን ትልቅ አቅም በማስተባበር ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን እናጠናክራለን ሲሉ ተናግረዋል።

የአስተዳደሩን ራዕይ በመጋራት ለበጎ አገልግሎት ድጋፍ እያደረጉ የሚገኙ ባለሀብቶችን ያመሰገኑት ከንቲባዋ፤ ባለሀብቶች ሕዝብን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ሥራዎች በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሙባረክ ከማል በበኩላቸው፤ አቅም ላነሳቸው ዜጎች የተገነቡት ቤቶች የነዋሪዎችን ችግር የሚቀርፉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ክፍለ ከተማው በ2015 በጀት ዓመት ሁለት ሺህ 200 ቤቶችን በማደስ አቅም ላነሳቸው ነዋሪዎች ማስረከቡን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ጠቁመው፤ የበጎ ፈቃድ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሰዒድ ዓሊ በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ በመንግሥትና በአልሚ ባለሀብቶች ትብብር የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ የቤት ችግር የሚያቃልሉ ቤቶች ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በአዲሱ ዓመት በክፍለ ከተማው 264 ቤቶችን በመገንባት ለዜጎች ለማስተላለፍ ዝግጅት መደረጉን አመላክተዋል።

የሚገነቡ ቤቶች የክፍለ ከተማውን ገፅታ የሚቀይሩ ናቸው ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ በቤቶቹ ግንባታ ሂደት ሃላፊነታቸውን ለተወጡ አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በቤት ግንባታ ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ተፈራ ዘውዴ በበኩላቸው፤ ከዚህ ቀደም ይኖሩነት የነበረ ቤት ደሳሳና ለኑሮ አመቺ አለመሆኑን ተናግረው፤ አሁን ላይ በተሻለ ጥራት የተሰራላቸው ቤት አዲስ ዓመትን በደስታና በተስፋ እንዳሳልፍ ያደርገኛል ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የአካል ጉዳተኛና የአቅመ ደካሞችን ችግር በመመልከት ለሰራው መልካም ሥራ ያመሰገኑት አቶ ተፈራ፤ በቀጣይ መሰል ችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የሚደረገው እገዛ እንዲጠናከር ጠይቀዋል።

ሌሎች የቤት ዕድለኞች ከተማ አስተዳደሩ በቤት ግንባታ ላደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል። ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለቤት ዕድለኞቹ የበዓል ማዕድ አጋርተዋል።

# በክልሉ በተያዘው በጀት ዓመት 27 ቢሊዮን ብር የሚገመት የዜግነት አገልግሎት ተከናውኗል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በዘንድሮ በጀት ዓመት 27 ነጥብ 67 ቢሊዮን ብር የሚገመት የዜግነት አገልግሎት መከናወኑን የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ገለጸ፡፡

የኦሮሚያ ገንዘብ ቢሮ ሃላፊና የበጎ ፍቃድ አግልግሎት አስተባባሪ ዶ/ር መሀመድ ናስር አባ ጀማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በ2011 ዓ.ም ጨፌ ኦሮሚያ ማንኛውም ዜጋ በሀገሪቱ ልማት ውስጥ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክትና ማንኛውም ልማት የመደገፍ ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ደንግጓል፡፡ በዚህም ዜጎች የሚያስፈጓቸው ልማቶች የመንግሥትን በጀት ሳይጠብቅ በራሱ እያከናወነ ይገኛል ብለዋል፡፡



ዶ/ር መሀመድ ናስር አባ ጀማል

ዶ/ር መሀመድ በክልሉ የበጀት ዓመቱ ከተጀመረ በዜግነት አገልግሎት 27 ነጥብ 67 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሥራ በተለያየ ዘርፍ መሠራቱንና በዚህም 21 ሚሊዮን ሰዎች መሳተፋቸውን ገልጸዋል፡፡

ክልሉ በ43 ዘርፍ የዜግነት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በዚህ ክረምትም በችግኝ ተከላ፣ በትምህርት ቤቶች ግንባታና ደረጃ ማሻሻል ፣የጤና ተቋማት ግንባታ፣ የደም ልገሳና የአቅመ ደካማዎች ቤት እድሳት ላይ በስፋት መሠራቱን ገልጸዋል፡፡

ከሀምሌ ወር ጀምሮ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን የገለጹ ሲሆን በክልሉ ከተተከሉ ችግኞችም አብዛዎቹ በዜግነት አገልግሎት አማካኝነት የተከናወኑ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ክልሉ በእያንዳንዱ ቀበሌ ቢያንስ አንድ ቅድመ ትምህርት ቤት ሊኖር ይገባል ብሎ እየሠራ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 4574 ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለመሥራት ታቅዶ እስካሁን ድረስ ሁለት ሺ ቅድመ ትምህርት ቤቶች መገንባቱን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከደረጃ በታች ያሉ ትምህርት ቤቶች በ15 ዘርፎች ላይ የማሻሻል ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው በዚህም 3 ሺ 410 ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ እስካሁን 2 ሺ 771 ትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ዶ/ር መሀመድ ከትምህርት ቤቶች በተጨማሪ አቅም የሌላቸው ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዳይለዩ ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን ሁለት ነጥብ አምስት ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ እስካሁን አንድ ሚሊዮን ለሚሆኑ ተማሪዎች የትምህርት መርጃ ግብዓቶች መዳረሱን ገልጸዋል፡፡

በዜግነት አገልግሎት መርሀ ግብር በዘንድሮው በጀት ዓመት በተለየ መልኩ የእናቶችን ድካምና ጫና ለመቀነስ ትኩረት መሰጠቱን የገለጹት አስተባባሪው የእናቶች የጉልበት ሥራን ለመቀነስ 7 ሺ ለሚሆኑ እናቶች ጋሪና አህያ የመስጠት እንዲሁም ለ አንድ ሺ 31 እናቶች የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ላሞች መስጠት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

# “ጳጉሜን ለኢትዮጵያ”

## በሚል በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የንቅናቄ ሥራ ይከናወናል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- “ጳጉሜን ለኢትዮጵያ" የንቅናቄ ሥራዎች በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች እንደሚከናወን የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) በወቅታዊ ጉዳይ መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸውም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከበረውን "ጳጉሜን ለኢትዮጵያ" ንቅናቄ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች በስፋት እንደሚከናወን ገልጸዋል።

ጳጉሜን ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት መሸጋገሪያ ድልድይ ተደርጎ እንደሚወሰድ አንስተው፤ በስድስቱ ቀናት ክልሉ ካለበት ችግር እንዲወጣ የምንሠራበት፣ ወደልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎቻችን የምንገባበት፣ እርስ በእርስ የምንመካከርበት፣ በሰከነ መንፈስና በመከባበር ተመስርተን ከችግሮች ለመውጣት የምንሠራበት ጊዜ ነው ብለዋል።

ያለፉትን ፈተናዎች እንደ ትምህርት በመውሰድ ቀጣይ ችግሮችን ፈትተን ፈተናዎችን ተሻግረን ወደ ተሟላ ቁመና የምንሸጋገርበት መሆን አለበትም ሲሉ ተናግረዋል።

የጳጉሜን ቀናት መነሻ በማድረግ ዓመቱን ሙሉ በትጋት እንሠራለን ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ በክልሉ በርካታ አካባቢዎች ሰላምን የማምጣት ሥራ መሠራቱንና የልማት ሥራዎችም እየተከናወኑ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር መዘጋጀታቸውንና ተማሪዎች ምዝገባ እያከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

ቢሮ ኃላፊው እንደገለጹት፤ የጤና ተቋማት መከላከልን መሠረት አድርጎ የጤና ሥራ እያከናወኑ ይገኛል። በግብርና ምርት ከራስ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ምርት እንዲኖር ጥረት እየተደረገ ነው

በጳጉሜን አንድ የአገልጋይነት ቀን የሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ የሚሰጥበትና ከአሁን በፊት ሕዝብ ያማረሩ፣ ተገቢውን ግልጋሎት በመስጠት የሚፈቱበት እንደሆነ አመላክተዋል።

በሁለተኛው የጳጉሜን ቀን የመስዋዕትነት ቀን በመሆኑ ለፀጥታ ተቋማት ልዩ ክብር የሚሰጥበት፣ ጀግንነት የሚዘከርበትና ከፀጥታ ተቋማት ጋር የምንቆምበት ነው ያሉት ኃላፊው፤ ለቀጣዩ ትውልድ ጀግንነት የሚወረስበት ነው ብለዋል።

በሦስተኛው የጳጉሜን ቀን ደግሞ በጎነት የሚታይበትና የሚዘከርበት መሆኑንም ተናግረዋል። ጳጉሜን አራት ቀን ደግሞ በአምራችነት ቀን የሕዝባችን ታታሪነትና ሥራ ወዳድነት በመዘከር ከእራስ አልፎ ለሌሎች እንዴት ተስፋ መሆን እንደሚቻል የሚዘከርበት ዕለት መሆኑን ጠቁመዋል።

ጳጉሜን አምስት በትውልድ ቀን ኢትዮጵያን አፅንቶ ያኖረው፣ አሁንም የተረከባት ትውልድ የሚዘከርበት ቀን ነው ብለዋል። አወንታዊ ነገሮችን በማጉላትና ለቀጣዩ ትውልድ በማስተማር በአሉታዊ ጉዳዮች ደግሞ ትምህርት በመውሰድ ቀኑ እንደሚታወስ አመላክተዋል።

የአብሮነት ቀን በሚከበርበት ጳጉሜን ስድስት ቀን ደግሞ የአብሮነት ታሪካችን የሚገለጥበት ቀን ነውም ብለዋል።

ልዩነቶችን በማቻቻል አንድ የምንሆንበት፣ ፍቅርን የምንሰብክበት፣ መቻቻልን የምናመጣበት፣ በሰላም መኖርን የምንዘክርበት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በጳጉሜን ቀናት ፍቅርን መስበክ፤ አንድነትን ማጠናከር ይገባልም ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በፍቅርና በአንድነት መኖር የሚያስችሉ ሁነቶች እንደሚካሄድባቸውም ገልጸዋል።

በየደረጃው ያሉ መሪዎች ጳጉሜን በተገቢው መንገድ እንዲያከብሩም አሳስበዋል። በቀጣይ ዓመት የተሻሉ ሥራዎችን ለመሥራት መዘጋጀት እንደሚገባም አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝብን ማገልገል ክብር ነው!

ሕዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤት ነው። የሕዝብን የስልጣን ባለቤትነት አምነው የተንቀሳቀሱ ሀገራት በእድገት ተመንድገው፤በዴሞክራሲ አብበው ታይተዋል። ሕዝብን ለማገልገል እንጂ በሕዝብ ለመገልገል ፍላጎቱ የሌላቸው አገልጋዮች ያሏቸው ሀገራት ማኅበራዊ እርካታን ከማረጋገጣቸው ባሻገርም ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባቸው ናቸው።

በማንኛውም መንገድ ሕዝብ መደመጥን ይፈልጋል። ለጥያቄዎቹ ተግባራዊ ምላሽ ይሻል፤ ካልሆነም ጥያቄዎቹ ምላሽ ያላገኙበትን ተጨባጭ ምክንቶች ማዳመጥን ይፈልጋል። ይህ ካልሆነ ሰሚ እንዳጣና ተገቢው ክብር እንዳልተሰጠው ሊቆጥር ይችላል። ይህ ደግሞ የመጨረሻ ውጤቱ የመልካም አስተዳደር ችግር ይሆናል።

በተለይም በዚህ የቴክኖሎጂና የግሎባላይዜሽን ዘመን ከሕዝብ ፍላጎት በተጻራሪ ቆሞ የስልጣን ዘመንን ማራዘም ከማይቻልበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። የእያንዳንዱ ዜጋ ድምፅ ዋጋ እንዳለው ሁሉ፣ የእያንዳንዱ ዜጋም ጥያቄ ዕውቅና መስጠት ሊታለፍ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።ከሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ተቀባይነት እያጡ፣ በሕዝብ ይሁንታ ላይ የተመሠረቱ ውሳኔዎች ተቀባይነት እያገኙ መሄድ ጀምረዋል።

ኢትዮጵያም የዓለም አንድ አካል ናትና ይህን እውነታ መጋራቷ አይቀርም። በርግጥ ኢትዮጵያ ለዘመናት በንጉሳዊ፤ በወታደራዊና ከዚያም ቀጥሎ በመጣው ቡድን ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ስር በመቆየቷ የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ባህል ገና አልጎለበተም። በሕገ መንግሥት ደረጃ ዜጎች ከመንግሥት ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው ቢገለጽም በተግባር ብዙ ርቀት የሚቀረው ነው።

በእርግጥ እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ሀገራት ይቅርና ባደጉትም ሀገራት ቢሆን ሁሉንም የሕዝብ ፍላጎት ማሳካት አይቻልም። ሆኖም የታቀደው ነገር ያልተሳካበትን ሁኔታ መግለጽና ለሕዝብም ተገቢውን መረጃ መስጠት ግን የሕዝብ አገልጋይነትንና ቅንነትን መላበስን እንጂ በኢኮኖሚ ማደግን ፤ በቴክኖሎጂ መገስገስን አይጠይቅም። ዋናው ነገር የሕዝብ አገልጋይነት ስሜትና ቅንነት ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ብዙ ቅን አገልጋዮች አሏት። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሕዝብን በቅንነት የሚያገለግሉ፤ በምልጃና በጉቦ የማይደለሉ፤ ለዘመድ አዝማድ አድልኦ የማይፈጽሙ አገልጋይ ዜጎች ያሏት ሀገር ናት። በትራንስፖርት ዘርፉ፣ በጤናው መስክ፣ በፀጥታና ደኅንነት ሙያ፤ በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎትና በመሳሰሉት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለሕዝብ ኖረው ለሕዝብ የሚሞቱ አገልጋዮችን መቁጠር ይቻላል።

ከዚሁ በተጻራሪ ግን አንዳንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎቶቻቸው ሲስተጓጎሉ ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም ብለው የሚቀመጡ፤ በማን አለብኝነትና በምንቸገረኝነት የሚያልፉና ምንም አይነት ሕዝባዊ ተቆርቋሪነት የማይታይባቸው ናቸው።

መንግሥት ለሁሉም ዜጎቹ ባለበት ኃላፊነት መሠረት ለሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። ዜጎች እንግልት ደረሰብን፣ በሙስናና ብልሹ አሠራር ተሰቃየን ፣ ውጣ ውረዱ አንገላታን የሚሉ አቤታዎችን ማዳመጥና ይህንኑ ተግባር የፈጸሙ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ እርምጃ መወሰድ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዛ በመለስ ቢያንስ ለተስተጓጎሉ አገልግሎቶች ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ ግን ሊለመድ የሚገባው አሠራር መሆን አለበት።

ይህ ሲሆን በሕዝብና በመንግሥት መካከል መተማመን ይኖራል። የመንግሥት ዕቅዶች የመተግበር አቅማቸው ያድጋል፤ልማት ይፋጠናል፤ብልሹ አሰራር ይቀንሳል፤ የዜጎችም ሕይወት ይለወጣል።

የዛሬውንም የአገልጋይነት ቀንም በተለያዩ ሙያ ላይ ተሰማርተው ኢትዮጵያን እያገለገሉ ያሉ አገልጋዮች የሚመሰገኑበትና ከፍ የሚሉበት ነው። በርካታ ተቋማትም በራቸውን ከሌሊቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ለተገልጋዮች ክፍት አድርገው ይጠብቃሉ። ስለዚህም በዛሬው ቀን ስለ አገልጋይነት አስበን ስንውል አገልጋይነት ያለውን ክብርና ሀገራዊ ፋይዳ በመረዳት መሆን ይኖርበታል። አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ሕዝብን ማክበር ባህል ሊያደርጉት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አዲሱን ዓመት በተስፋ እና በሥራ ስመቀበል

በምስጋና ፍቅሩ

አዲስ ዓመት ሊገባ በጣት የሚቆጠር ቀናት ናቸው የቀሩት።የክረምት ወቅት አልቆ ለብርሃናማው በጋ ሊለቅ በዝግጅት ላይ ነው።ምድሪቱም በአደይ አበባ ፍክት ብላ ፣አምራ እና ደምቃ ስትታይ አዲስ ዓመትን በተስፋ እንድንቀበለው አንዳች መልዕክት ትሰጣለች። «እንኳን አደረሳችሁ።» ለመባባል የቀሩን ቀናቶች ናቸው።

አዲስ ዓመት መጣሁ መጣሁ እያለ ባለበት በዚህ ወቅት በተሰነባቹ ዓመት ያየነው፤ ለአዲሱ ዓመት መሻገር ያለባቸውን ፣ መታረም እና መበረታታት አለባቸው ያልናቸውን ሀገራዊ ጉዳዮቻችንን በዚህ ፅሁፍ በወፍ በረር ለመቃኘት ሞከርን።

በቅድሚያ ባለፈው ዓመት ከዛም በፊት የሀገር ዋነኛ ፈተና የሆነው የሰላም ጉዳይ ነው ።በአንድም ይሁን በሌላ ይህ ችግር ዋጋ ያላስከፈለው ዜጋ አለ ብሎ ለማለት የሚያስደፍር ነገር የለም።

ሰላም በዜጎች የእለት ተእለት ህይወት ውስጥ ካለው የጎላ ስፍራ አንጻር የሰላም እጦቱ እንደ ሀገር ከፍ ላለ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳርጎናል። ዜጎች በሠላም ወጥተው እንዳይገቡ ፤ያሻቸው ቦታ ሄደው ሠርተው፣ ነግደው ፣ ኑሯቸውን እንዳይመሩ ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል።

በያዝነው ዓመት በፕሪቶሪያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት በሕወሓት እና በመንግሥት መካከል የነበረው ጦርነት በሰላም ስምምነት መቋጨቱ የሚበረታታ ነው። ስምምነቱን ተከትሎም ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል፤ ብዙ ጉዳዮችን ተስፋ እንድናደርግ አስችሎናል።

እንደ ሀገር ከጦርነቱ ምንም አላተረፍንም። ይልቁንም ወደኋላ ተጎተትንበት፣በገንዘብ ከሰርን፣ የበርካቶችን ወንድም እህቶቻችንን ሕይወት አጣን።አካል ጉዳት የደረሰባቸው ጥቂቶች አይደሉም።ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው የከፋ ሕይወት ለማሳለፍ የተገደዱም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው።

አሁን በሁለት ወገን የነበረው ጦርነት አብቅቷል። ዛሬ ላይ ሰዎች እንዴት መረዳት እንዳለባቸው፣ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎችም ተማሪዎቻቸውን ለመቀበል ጥሪ እያደረጉ፤ ዳግም ተከፍተው አገልግሎት ለመስጠት እየተዘጋጁ ነው። ይህ ሲሆን እንደመስማትም ሆነ እንደ ማየት ምን የሚያደስት ነገር አለ? ይህንን በአዲሱ ዓመት ተግባራዊ ሆኖ እንደምናየው ተስፋ አደርጋለሁ።

በአማራ ክልል ያለው የፀጥታ ችግር በአንድም ይሁን በሌላ እልባት እንዲያገኝ እየተሠራ ነው። ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከጅምሩ አንስቶ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች የሚበረታቱ ፣ እውቅና የሚሰጣቸው ናቸው።ይህንኑ አጠናክሮ በአዲሱ ዓመት መቀጠል ያስፈልጋል። ከግጭቱ ሊያተርፍ የሚችል አካል ካለመኖሩ አንጻር ከትናንት ተሞክሯችን መማር ተገቢ ነው።

በኦሮሚያ ክልል ያለውን የሰላም ችግር ለመቅረፍ የተጀመሩ ጥረቶች ፍሬ አፍርተው በክልሉ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ፣ ከዚህ ቀደም የተጀመሩ ጥረቶች ፍሬ እንዳያፈሩ አሉታዊ ተጽእኖ የነበራቸው አካላት እራሳቸውን በአግባቡ በማየት ወደ ሰላም ሊመጡ ይገባል።

ሌላው የሚመጣው ዓመት ትልቁ ሥራችንና ተስፋችን በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል የተጀመረው ሥራ ነው። በሀገሪቱ እዚህም እዛም የሚታየውን የሰላም መደፍረስ ለማጥራት ብሎም ችግሮቻችንን በንግግር እና በውይይት ለመፍታት ሁነኛ እድል ነው።

ይህንን እድል በአግባቡ መጠቀም ለመጪዎቹ ትውልዶች ባለ ትልቅ ውለታ መሆን ነው ።ይህንን እውነታ ታሳቢ አድርጎ በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስም የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው።

የኑሮ ውድነቱ ዕለት ዕለት እየፈተነን ይገኛል።በመንግሥት በኩል ፈተናውን ለማቅለል ብዙ ሥራዎች ቢሰሩም ይህ ነው የሚባል ለውጥ እያየን አይደለም። በዚህም ምክንያት የብዙዎች ሕይወት ለፈተና ተዳርጓል። ለዚህ ችግር ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ከመንግሥት ይጠበቃል።

**በአዲሱ ዓመት ሰላምን ዘርተን ሰላምን ስማጨድ ያብቃን፤ አዲስ ዓመት፤ አዲስ ተስፋ የምናይበት፤ መልካሙን ሁሉ የምንሰማበት ያድርግልን፤ በእኩልነት፣በመከባበር እና በመፈቃቀር የምንኖርበትን አዲስ የአስተሳሰብ መሠረት ያልብሰን**

በትምህርት በኩል ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ እየተደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴዎች በበጎ ማንሳት ይቻላል። የተለያዩ ሪፎርሞች ተደርገዋል። ያሉ ድክመቶችን በማረም ጠንክሮ ከተሠራ ብቁ፣ተወዳዳሪ እና በራሱ የሚተማመን ዜጋን ለሀገር ማፍራት ያስችላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

ነገር ግን በትምህርት ቤቶች ላይ እየታየ ያለውን በማን አለብኝነት የሚደረገውን የትምህርት ቤት ክፍያ ጭማሪ፤የእለት ጉርሱን ለማግኘት ለሚጨነቀው ወላጅ መርዶ እንደማርዳት ያህል ከሆነ ውሎ አድሯል።

መንግሥትም በችግሩ ዙሪያ ጣልቃ በመግባት ችግሩን ለመቅረፍ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። የወላጆችን አቅምና አጠቃላይ የሆነውን ሀገራዊ እውነታ ያገናዘበ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ይኖርበታል። በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለማስተማር የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆንም የመጽሐፍት እጥረቱን ከወዲሁ ማጤን ተገቢ ነው።

በፀጥታ መደፍረስ፣ በተፈጥሮ እና በሌሎች ምክንያቶች የተፈናቀሉ ዜጎች ከመርዳት አንጻር በርከት ያሉ ሥራዎች የተሠሩ ቢሆንም፤ ሥራዎቹ ከችግሩ ስፋት አንጻር በቂ ሆነው አልተገኙም።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት መንግሥትም ሆነ መላው ሕዝብ በአዲሱ ዓመት በኃላፊነት መንፈስ በመንቀሳቀስ የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል፤ የዜጎችን ችግር በጋራ እና በትብብር መንፈስ መፍታት የአዲሱ ዓመት ተቀዳሚው የቤት ሥራችን መሆን ይጠበቅበታል።

ሙሰኝነት ፣ ሌብነት የሕፃናት ሥርቆት እና ወዘተ በ2015 ዓ.ም ከሰማናቸው ዜናዎች መካከል ይጠቀሳሉ።ምንም እንኳን በፀጥታ ኃይል (ፖሊስ) በኩል ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ቢታወቅም ያለ ጉቦ ሥራቸውን የማይሠሩ ባለሙያዎች እየበዙ ፣ በተለያዩ መንገዶች በግለሰብ ሆነ በቡድን ደረጃ የሚከናወኑ ወንጀሎች እየሰፉ እንጂ እየቀነሱ አይደለም።ችግሩን ለመቆጣጠር በአዲሱ ዓመት ሕዝቡና የፀጥታ አካላት ተናበው ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ለአብነት ያህል የተወሰኑትን አነሳን እንጂ ፣በመጪው አዲሱ ዓመት ወገባችንን አጥብቀን ጥርሳችንን ነክሰን የምንሰራቸው ብዙ ሥራዎች እንደሚጠብቁን ይታመናል። ሥራዎቹ ስኬታማ እንዲሆኑ ታዋቂ ሰዎች፣ ምሁራን፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ እና ሌሎች ተሰሚነት ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ለዚህም በቂ ዝግጁነት እንደሚኖራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

እየመጣ ያለውን አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ ጽሑፌን በምርቃት ልቋጨው፤ በአዲሱ ዓመት ሰላምን ዘርተን ሰላምን ለማጨድ ያብቃን፤ አዲስ ዓመት፤ አዲስ ተስፋ የምናይበት፤ መልካሙን ሁሉ የምንሰማበት ያድርግልን፤ በእኩልነት፣በመከባበር እና በመፈቃቀር የምንኖርበትን አዲስ የአስተሳሰብ መሠረት ያልብሰን።አሜን!

**መልካም አዲስ ዓመት**

# ‹‹ፍርድ ቤቶች ለሕገወጥ መሬት ወራሪዎች የሚሰጡት ዕግድ ለሥራችን እንቅፋት ሆኖብናል››



- ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ
የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ

ሙሉቀን ታደገ

**ለአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን በሕግ ከተሰጡት ኃላፊነቶች መካከል ሕገ ወጥ ግንባታ መከላከል፣ ሕግ ወጥ የጎዳ ላይ ንግዶችን መቆጣጠርና ማስቆም ብሎም ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ እና ከሕግ ያፈነገጡ አሠሮራችን መከላከል ዋና ዋና ሥራዎቹ ናቸው። በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በዛሬው የተጠየቅ ዓምድ ዕትማችን ባለሥልጣኑ እነዚህን ኃላፊነቶቹን ከመወጣት አኳያ ምን እየሠራ ነው? ምን ምን ጉዳዮችስ እየፈተኑት ነው? ቀጣይስ ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን በምን መልኩ እየሠራ ነው? በሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።**

**አዲስ ዘመን፡- የባለሥልጣኑ ከተሰጠው ተቋማዊ ተልዕኮ አንጻር የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ በምን ደረጃ የሚገለጽ ነው?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን በአዲስ አበባ እንደሚገኝ እንደማንኛውም አገልግሎት ሰጭ ተቋም በተለይ በ2015 ዓ.ም በከተማዋ ውስጥ የሚታዩትን የደንብ ጥሰቶችን ለመከላከል፣ ለማረም፣ ለማስተካከል እና እርምጃ ለመውሰድ በርካታ እቅዶችን በማቀድ ወደ ስራ ገብቶ ነበር።

የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመትን እቅድ ከመውጣታችን በፊት በ2014 ዓ.ም ያቀድናቸውን እቅዶች በዝግጅት ምዕራፋችን በደንብ ተመልከተናል። በዚህም በ2014 ዓ.ም የከተማ አስተዳደሩ በሰጠን የሥራ ኃላፊነት ምን ሰርተናል? ምን ቀረን? የሚሉትን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖቻችንን ገምግመናል።

በዚህም ለ2015 ዓ.ም ሥራዎቻችን ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ጨምረን እና ቀንሰን የተሻለ ሊያሠራ የሚችል የተቋሙን መሪ እቅድ አውጥተን ወደ ሥራ ገብተን ነበር። ከመሪ እቅዱም ባሻገር ከአስራ አንዱ ክፍለ ከተሞች ባህሪ እና አቀማመጥ ጋር አያይዘን እቅድ አውጥተን አገልግሎት የሰጠንበት፤ ይህም ብቻ ሳይሆን 23 ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት በርካታ ሥራዎች ሠርተናል።

በከተማዋ የሚታዩ ችግሮችን በጋራ መፍታት እንደየተቋሞች እና እንደየቢሮዎች በአዋጅ የተሰጡ የሥራ ኃላፊነቶች መሠረት ያደረገ በመሆኑ የደንብ ማስከበር ከ23ቱ ተቋማት ጋር ለመሥራት የሚያስችሉ እቅዶችን አውጥተን ወደ ስራ ገብተን ነበር። በእቅዱ ዙሪያ ከህብረተሰቡ እና ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር ተወያይተናል።

ከእነዚህ መሥሪያ ቤቶች ጋር በምንሠራበት ጊዜ ምንድን ነው ተጋግዘን መሥራት ያለብን? ተቋሙስ የተሰጠው ተልዕኮ እንዴት ሊወጣ ይችላል? በሚሉት ላይ አትኩሮት ሰጥተን ሰርተናል። በዚህ መልኩም ወደ ትግበራ በመግባቱ ተቋሙ በ2014 አመርቂ ሥራዎችን መስራት ችሏል። ይህን የተሻለ አፈጻጸም ደግሞ በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ማስቀጠል አለብን ብለን ገምግመናል። በግምገማው መሰረት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሻለ እንደነበር ማሳያዎቹ ምንድን ናቸው? ከዚህ በፊት ከነበሩት አሰራሮቻችን ምን የተለወጠ ነገር አለ? የሚለውን በደንብ አይተናል።

አንድ ተቋም ደግሞ በአዋጅ እና መመሪያ ተቆጥሮ የሚሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም የተቋም ግንባታ እና አደረጃጀት ወሳኝነት አለው። ከዚህ አኳያ ባለሥልጣኑ የተቋም ግንባታው ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ከሙያተኞች እና ከአመራሮች ጋር በመቀናጀት ተቋማችንን ለመገንባት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ በተቋሙ ከተሠሩ ሥራዎች መካከል የተሰጡንን ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል ደንብ ማርቀቅ ነው። ከዚህ አንጻር በ2015 ዓ.ም ደንብ አርቅቀን በሕዝብ በማስተቸት እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት አዋጅ 74/2014 የሚያጠናክር የደንብ ቁጥር 150/2015ን አጸድቀን ወደ ሥራ ገበተናል።

ደንቡን ሊያሠራ የሚያችሉ ሦስት የሥራ መመሪያዎችን አውጥተናል። ደንብ እና ሕግ የተሻሻለ እና የጠነከረ ከሆነ ተጠያቂነትም ይኖራል፤ ፍትሐዊነትን ማስፈን ይቻላል። ከዚህ አንጻር ባልስልጣን መሥሪያ ቤቱ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በትክክል እንዲወጣ የሚያስችሉ ደንብ እና መመሪያዎችን አውጥቷል።

ሌላው በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ከተሠሩ ዐብይ ጉዳዮች መካከል ከፐብሊክ ሰርቪስ ጋር በመሆን በቢፒአር ጥናት መሻሻል ያለባቸውን ሥራዎች አሻሽለን ወደ ሥራ ገብተናል። በተቋሙ በርካታ የሲቪል ሠራተኞች አሉ። እነኚህ የሲቪል ሠራተኞች በፍላጎት እና በሞራል እንዲሠሩ የደረጃ እድገት እንዲያገኙ ተደርጓል።

በተለይም ከዚህ ቀደም የፓራ ሚሊቴሪ የተቋሙ ሠራተኞች የደመወዝ የዕድገት ደረጃ ለውጥ የሌለው እና በነበረበት የቆመ ነበር። ይህንን ለማሻሻል በማሰብ፤ ሰው በየችሎታው እና በአገልግሎቱ ልክ ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኝ ኃላፊነቱ እና ተጠያቂነቱም እንዲጨምር ለማድረግ በሚል ከፐብሊክ ሰርቪስ ጋር በመተባበር የአፊሰሩን የሥራ እድገት እንዲያገኙ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከዚህ ባሻገር ፓራ ሚሊቴሪው ራሱን ችሎ ከከተማ ጀምሮ እስከወረዳ ድረስ የሚገኙ በመከላከል፣ በቁጥጥር እና እርምጃ ዘርፉ ውስጥ ያሉ የሥራ ሂደት እና አመራሮች በተቀናጀ ሁኔታ ከላይ እስከታች የዕዝ ሰንሰለቱ እየተሻሻለ እና ለግዳጅ አወጣጥ በሚያመች መልኩ እንዲደራጅ ያደረግንበት አሠራር አንዱ የተቋሙ ስኬት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የሚስተዋለውን የከተማ እድገትና የወንጀል መበራከት ተገንዝቦ ከመስራት አኳያ ምን ሠርታችኋል?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** ከተማችን እየሰፋች ከመሄዷ ጋር ተያይዞ የወንጀል አይነቶችም እየተበራከቱ መጥተዋል። እነኚህ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቀልበስ የሚያስችል ኃይል ማደራጀት በማስፈለጉ ከዚህ ቀደም ከነበሩን 5ሺ325 ነባር ኦፊሰሮች በተጨማሪ በዘንድሮው ዓመት ወደ 1ሺ110 ኦፊሰሮችን ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች መልምለን ወደ ሥራ ለማስገባት በሂደት ላይ ነን። በቅርቡ ተመርቀው ወደ ሥራ ይገባሉ። ይህ ኃይል ስልጠናውን ጨርሶ ወደ ነባሩ ሲቀላቀል የተሻለ የማስፈጸም አቅም ይፈጥርልናል።

ሁለተኛው ደግሞ ሥራችን ነው። በተቋሙ ከተሠሩ ሥራዎች አንዱ የሪፎርም ሥራ ነው። በዚህም የአገልግሎት አሰጣጣችን፣ የመልካም አስተዳደር፣ የብልሹ አሰራር እና የሌብነት እንቅስቃሴ ሥራዎችን በመቀልበስ እና የተሻለ ተቋም ሆኖ እንዲወጣ ለማድረግ ሥራዎች ተሰርተዋል። በዚህም በ11 ክፍለ ከተሞች የሚገኙ አመራሮችን ቀያይረናል። ከ60 በላይ የሚገመቱ የወረዳ አመራሮችን ለውጠናል። ከአንድ ሺህ በላይ ኦፊሰሮችንም ከነበሩበት ቦታ እየቀያየርን እንዲሰሩ አድርገናል።

በአባሎቻችን ላይ ከኅብረተሰቡ ዘንድ ሰፋ ያለ ቅሬታ በመኖሩ ይህን ቅሬታ ለመፍታት የኅብረተሰቡን ሃሳብ በመሰብሰብ እና በመጭመቅ እንደ ግብዓት በመጠቀም ለአባሎቻችን ስልጠና በማዘጋጀት በጥሩ ሥነ-ምግባር ኅብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ለማድረግ ተችሏል። ይሁን እንጂ አሁንም አልፎ አልፎ የሚታዩ የሌብነት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሉ።

> **ከትልልቅ ባለኮኮብ ሆቴሎች እስከ በመኖሪያ ቤቶች፤ ከሬስቶራንቶች እስከ ማሳጅ ድረስ ከኢትዮጵያዊነት ባህሪ ያፈነገጡ እና የአምራች ኃይሉን ሥነ አዕምሮ የሚያበላሹ ተግባራት ይከናወናሉ። ‹‹ኒኮቲን›› ያላቸው መርዛማ ሆኑ አደንዛዥ ዕጾችን ይጠቀልላሉ፤ ይሸጣሉ**

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ባለስልጣኑ በግልጽ ተለይተው የተሰጡት ሥራዎች አሉ?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ዘጠኝ የሥራ መደቦች እንዲያከናወን ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል። አንደኛው ከመሬት ጋር የተያያዘ ነው። እንደሚታወቀው መሬት የሀገር ሀብት ነው። ከዚህ አኳያ የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር በከተማዋ ውስጥ የሚታዩ ባዶ ቦታዎችን እንዲጠብቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በዚህ መሰረት የመንግሥትን መሬት ለግል ጥቅማቸው ሊያውሉ የተንቀሰቀሱ አካላት ላይ እርምጃ ወስዷል።

በዚህም 15ሺ 749 የሚሆኑ የተወረሩ መሬቶችን (ቦታዎችን) ለመንግሥት ማስልመስ ችሏል። የመሬት ወረራ ችግር በሁሉም የከተማ አስተዳደሩ ክፍለ ከተሞች የሚስተዋል ቢሆንም ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ቦሌ፣ ለሚ ኩራ እና ኮልፌ ቀራኒዮ ላይ ግን የበረታ ነው።

ሁለተኛው ተቋሙ ቁጥጥር ከሚያደርግባቸው ዘርፎች መካከል ሕገ ወጥ ግንባታ ነው። ከዚህ አንጻር በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ከተሰጣቸው ይዞታ ውጭ ግንባታ ባከናወኑ 8ሺ235 ሕገ ወጦች ላይ ተቋሙ እርምጃ ወስዷል። ሦስተኛው ከሕገወጥ የመሬት መስፋፋት ጋር የተገናኘ ነው። በዚህም ከተሰጣቸው ቦታ ውጪ ትርፍ ቦታ በመጨመር ለመገንባት የሞከሩ 2ሺ198 ሰዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል።

አራተኛው የጎዳና ንግድ ነው። ሕገ ወጥ የጎዳና ንግድ ስንል በእግረኛ መንገድ፣ በአደባባዮች፣ በተሽከርካሪ መንገዶች፣ ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ምርት የሚከናወን ንግድ ነው። ከዚህ አንጻር በተለይ በዘንድሮው ዓመት ወደ 82ሺ 824 የሚገመቱ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል። ተቋሙም ውጤት ካገኘባቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ ይሄ ነው።

አምስተኛው ደግሞ የእርጥብ እና ደረቅ ቆሻሻን መከላከል ነው። ከግለሰብ፣ ከተቋማት፣ ከኢንዱስትሪዎች ወዘተ የሚወጡ ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የሚለቁ አካላት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አድርገናል። በዚህም 9ሺ933 ሕገወጦች ላይ እርምጃ ወስደናል።

ሕገ ወጥ እርድ እና የእንስሳት ዝውውርን በተመለከተም፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በዚህ ዓመት 2ሺህ ዘጠኝ በሚሆኑ ሕገ ወጥ እርድ በፈጸሙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ ተወስዷል። ሕገ ወጥ የመንገድ አጠቃቀም ጋር በተያያዘም በተለይም የግንባታ ሥራዎች በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች በእግረኛ እና በተሽከርካሪ መንገዶች ላይ አሸዋ፣ ብረታ ብረት እና ድንጋይ የማከማቸት ተግባር ሲፈጽሙ ይታያል። በዚህም 20ሺ 543 ግለሰቦች ላይ እርምጃ ወስደናል።

ስምንተኛው እና ሌላው ኃላፊነት ደግሞ አዋኪ ተግባርን መቆጣጠር ነው። ከትልልቅ ባለኮኮብ ሆቴሎች እስከ በመኖሪያ ቤቶች፤ ከሬስቶራንቶች እስከ ማሳጅ ድረስ ከኢትዮጵያዊነት ባህሪ ያፈነገጡ እና የአምራች ኃይሉን ሥነ አዕምሮ የሚያበላሹ ተግባራት ይከናወናሉ። ‹‹ኒኮቲን›› ያላቸው መርዛማ ሆኑ አደንዛዥ ዕጾችን ይጠቀልላሉ፤ይሸጣሉ። ከዚህ በመነሳት 3ሺ792 ሕገ ወጦች ቤቶች ላይ እርምጃ ተወስዷል።

ሌላው ቁጥጥር እንድናደርግ ኃላፊነት የተሰጠን በሕገወጥ ማስታወቂያ ላይ ነው። በዚህም 392ሺ646 ሕገ ወጥ ማስታወቂያዎች እንዲነሱ ተደርጓል። በድምሩ በበጀት ዓመቱ 125 ሺህ 827 ሕገወጦች ላይ እርምጃ ወስደናል። ወደ ሕግ ከምናቀርባው ውጪ በገንዘብ ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ምን ተግዳሮቶች አጋጣማችሁ? እንዴትስ ፈታችሁ?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** በ2015 ዓ.ም በርካታ ችግሮች አጋጥመዋል። በተለይ በሥራ ላይ በነበሩ ኦፊሰሮች

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

ከገጽ 6 የዞረ

## ‹‹ፍርድ ቤቶች ለሕገወጥ መሬት...

ላይ ሕገወጦች በፈፀሙት ተግባር ከህይወት ማጣት እስከ አካል ጉዳት አጋጥሟል። በዚህም አንድ አባላችን በመኪና ተገጭቶ ሲሞት ከ10 በላይ የሚሆኑ አፊሰሮች ደግሞ የዓይን መጥፋት፣ የጥርስ መሰበር እና የአካል ጉዳት አጋጥሟቸዋል።

ሁለተኛ ከመሬት ጋር ተያይዞ አሁንም ቢሆን ሊሻሻል እና ሊስተካከል ያልቻለ በባዶ መሬት ወይም ባንክ በገቡ፤ በአርሶ አደር ወይም ግሪነሪ ቦታዎች ላይ አንድ ሕገ ወጥ ሥራ የሚሰራ ሰው ሕገወጥ ተግባሩን ከማከነወኑ በፊት ከሚመለከተው የፍትህ አካል ወይም ፍርድ ቤት እግድ ያወጣል። በዚህም ማታ ባዶ የነበረ ቦታ ጠዋት ስትነሳ በቆርቆሮ ታጥሮ እግድ ተለጥፎበት ታገኘዋለህ።

በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶች ለሕገወጥ መሬት ወራሪዎች የሚሰጡት እግድ ለሥራችን እንቅፋት ሆኖብናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አባሎቻችን ሕገ ወጥ ተግባሩ እንዴት ይፈጸማል? ሲሉ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተላልፋችኋል እየተባሉ አባሎቻችን እንዲታሰሩ እና እንዲንገላቱ እየተደረገ ነው።

አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ ያልተፈቱ እና በቀጣይ ትኩረት ሰጥታችሁ ልትሰሩባቸው የለያችኋቸው ችግሮች አሉ?

ሻለቃ ዘሪሁን፡- ትልቁ ያልተፈታ ችግር ብለን የገመገምነው ከመሬት ጋር የተያያዙ ችግሮች ናቸው። በእርግጥ አሁን ላይ የከተማ አስተዳደሩ የወሰዳቸው እርምጃዎች አሉ። እያንዳንዱ መሬት እንዲቆጠር ተደርጓል። እንዳንዱ ባዶ መሬት የመንግሥት የሆነ፣ የአርሶ አደር የሆነ፣ ተቆጥሮ ለደንብ ተላልፏል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በመሬት ላይ ያለው ፍላጎት በጣም ከባድ ነው። ከባድ እንደመሆኑ መጠን አሁንም አንዱ የከተማችን ችግር ወይም ተግዳሮት ከመሬት ጋር የተያዘ ችግር ነው።

ሌላው የተቋሙ ፈተና እና አሁን መቅረፍ አስቸጋሪ የሆነው የጎዳና ላይ ንግድ ነው። በጎዳና ላይ የሚነገዱ ንግዶች በከተማችን እንደ ባህል ተቆጥረዋል። ይህ ደግሞ ከከተማዋ ስታንዳርድ አኳያ ተገቢ እና ትክክል ያልሆነ ተግባር ነው ።

አዲስ ዘመን፡- በ2016 በልዩ ትኩረት ልትሰሩት ያሰባችሁት ምን አለ?

ሻለቃ ዘሪሁን፡- በ2016 ዓ.ም ለመስራት ከታቀዱ ሥራዎች መካከል የአባሎቻችን የሥነ ምግባር ሁኔታ በማሻሻል ዘጠኙን የደንብ ጥሰቶች በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ የሚለው ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ነው። ይህ ድርድር የሌለው ማድረግ የሚገባን ነገር ነው። በተቋማችን የሚታዩ የሥነ ምግባር ችግሮች፣ የሌብነት እና የብልሹ አሰራሮች ምንድን ናቸው የሚሉትን ለይተን እየሰራን ነው።

በዚህም በጣም ጫፍ የወጡትን ከተቋሙ እንዲቀነሱ ይደረጋል። መማር የሚችሉትን ደግሞ እናስተምራለን። ይህን ሥራ ከሠራን ሁሉ ነገር ቀላል ይሆናል። ፍትሐዊ አገልግሎት እና ለሕዝብ የሚኖር የአገልጋይነት ስሜት እያደገ ይሄዳል። በዚህም የተቋም ግባችንን ማሳካት ይቻላል።

አዲስ ዘመን፡- የተጠቀሱትን የተቋሙ ዓላማ ለማሳካት ከሰው ኃይል አኳያ ያላችሁ አደረጃጀት በቂ ነው ብለው ያስባሉ?

ሻለቃ ዘሪሁን፡- በተቋሙ ውስጥ በርካታ የሰው ኃይል አለ። የፓራ ሚሊታሪው ክንፍ አንደኛው ነው። በዚህም 5ሺ 325 የሚደርስ የሰው ኃይል የያዘ ነው። ይህ ክንፍ የተሻለ ሥራ እንዲሰራ ከአንድ ሺህ በላይ ሠራዊት አሰልጥነናል። በቅርብ ቀን ወደ ሥራ እንዲገባ ይደረጋል። ሌላው የሲቪል ክንፍ ነው። ይህ ክፍል በአብዛኛው በከተማ እና በክፍለ ከተማ ደረጃ ይገኛል። ካለን የሰው ኃይል ከ60 እከ 70 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ነው። ስምሪት ላይ ለሚገኘው ኃይል ድጋፍ የሚሰጥ ነው።

አዲስ ዘመን ፡- ከሰው ኃይል ምልመላ አንፃር የምትከተሉት መስፈርት ምንድን ነው? ማስታወቂያው ለሕዝብ ግልጽ አይደለም ይባላል። እርስዎ ምን ይላሉ?

ሻለቃ ዘሪሁን፡- እኛ የሰው ኃይላችንን ስናደራጅ ግልጽ የሆነ ማስታወቂያ እናወጣለን። መስፈርቶችም ኢትዮጵያዊ፣ ከወንጀል ነጻ፣ ለሕዝብ ታማኝ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ተወላጅ ወይም በከተማዋ ውስጥ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ የኖረ ወዘተ የሚሉ ናቸው። ስብጥሩም ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ነው። በአጠቃላይ የቅጥር ማስታወቂያዎች በተመለከተ



**ከሚወረሱ ንብረቶች ጋር ተያይዞ ንብረቶች ሁለት አይነት ናቸው። ለአብነት፣ በፍጥነት የሚበላሹ አትክልት እና መሰል ንብረቶች ይገኛሉ። ይህ በአፋጣኝ ይወገዳል። ኤሌክትሮኒክስ እና ጨርቃ ጨርቅ የመሰሉ ደግሞ ሲወረሱ ገቢ የሚደረግበት የራሱ መመሪያ አለው። በዚያ መሰረት ገቢ ይደረጋል**

በየክፍለ ከተማዎች ለሕዝብ ግልጽ በሆኑ ቦታዎች እንዲለጠፉ ይደረጋል።

በሲቪል ክንፉ ደግሞ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሰረት ቅጥር ይከናወናል። ከትምህርት ዝግጅት አንጻር በተለይ በአሁኑ ዓመት ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የሆነ ነው። ከጾታ አንጻር የሴቶችን ተሳትፎ ከወንዶች እኩል ለማደረግ እየተሠራ ነው። በዚህ ዓመት በተከናወኑ ምልመላዎች 48 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው ። በቀጣይ እኩል ለማድረግ ይሠራል።

አዲስ ዘመን፡- ከሕገወጦች ከሚወረሱ ንብረት አያያዝ እና አስተዳደር ጋር ግልጽነት ይጎድላል የሚል ቅሬታ ከኅብረተሰቡ ይሰማል፤ በተጨማሪም ጉዳዩን ለሕዝብ እና ለሚዲያዎች ከማሳወቅ አንጻር ምን ያህል ተባባሪ ናችሁ?

ሻለቃ ዘሪሁን፡- የሠራናቸውን ሥራዎች ለሕዝብ እና ለሚዲያ ከማሳወቅ አንጻር በአዲስ አበባ ከሚገኙ ተቋማት የደንብ ማስከበር ግንባር ቀደም ነው። አብዛኛው ሥራችን በሚዲያ የተደገፈ ነው። በተቋሙ የተደረጉ የሥራ ክንውኖችን ለሚዲያ ያላሳወቅንበት ጊዜ የለም። በዚህም ሥራችንን ለሕዝብ ግልጽ እያደረግን መጥተናል። በዚህም በእኛ ተቋም ተሠርተው ሕዝብ የማያውቃቸው ሥራዎች የሉም።

ከሚወረሱ ንብረቶች ጋር ተያይዞ ንብረቶች ሁለት አይነት ናቸው። ለአብነት፣ በፍጥነት የሚበላሹ አትክልት እና መሰል ንብረቶች ይገኛሉ። ይህ በአፋጣኝ ይወገዳል። ኤሌክትሮኒክስ እና ጨርቃ ጨርቅ የመሰሉ ደግሞ ሲወረሱ ገቢ የሚደረግበት የራሱ መመሪያ አለው። በዚያ መሰረት ገቢ ይደረጋል።

በወረዳ ደረጃ በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚመራ የጨረታ ኮሚቴ አለ። የደንብ ማስከበር ከኮሚቴው ውስጥ አንዱ አባል ነው። ሻጭ ግን አይደለም። የተወረሱ ንብረቶችም በወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መሪነት በጨረታ ሕግ እና ደንብ መሰረት በግልጽ ጨረታ ተሽጦ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የደንብ ማስከበር ፈተናዎች አሉበት። ከእነዚህም መካከል የሚወረሱ ንብረቶችን ማስቀመጫ ቦታዎች ማጣት አንዱ ነው። ይህ ደግሞ ለሌብነትም ሆነ ለብልሹ አሰራር ክፍት ያደርገዋል። እንደዚህ አይነት ችግሮችን ለማረም በ2016 የበጀት ዓመት ከፍተኛ ሥራዎችን ለመስራት እቅዶች ተዘጋጅተዋል።

አዲስ ዘመን፡- ከደንብ ማስከበር አፊሰሮች ጋር ተያይዞ የሥነ ምግባር ችግር መኖሩን የተለያዩ አካላት ያነሳሉ። በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?

ሻለቃ ዘሪሁን ፡- ከአፊሰሮቻችን ጋር በተያያዘ ከኅብረተሰቡ ዘንድ የሚነሱ ሃሳቦች ፣ጥቆማዎች አሉ። እንደ ተቋም ከኅብረተሰቡ ዘንድ የሚነሱ ሃሳቦች፣ ጥቆማዎች ትክክል ነው ብለን እናምናለን። ምክንቱም ሕዝብ ስለማይሳሳት። እኛ የማናያቸውን በተለይ አፊሰሮቻችን ከሕዝቡ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ እንደመሆኑ መጠን የተቋሙ አመራሮች ከሚቆጣጠሩት በላይ ሕዝቡ በደንብ ያያቸዋል።

ከሕዝብ በሚሰጠን ጥቆማ እና አመራሩ በሚያደርገው ክትትል መሰረት በ2014 ዓ.ም የደንብ ማስከበር አፊሰሮች የሥነ ምግባር ችግር ጎልቶ የወጣበት እና አስቸጋሪ የሆነበት ዓመት ነበር። በዚህም ተቋሙ በከፍተኛ ደረጃ የተፈተነበት ነበር። ይህን ለማስተካከል በ2015 ዓ.ም በጣም በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። ይሁን እንጂ አሁንም የሚታዩ ችግሮች አሉ።

በደረሰን ጥቆማ መሰረት ከሦስት በላይ የሚሆኑ አመራሮች እና ስድስት አፊሰሮች ከሌብነት እና ከብልሹ አሰራር ጋር በተጨባጭ ተገኝተዋል። እነዚህ ወደ ሕግ ቀርበው ከሥራም እንዲታገዱ ተደርጓል። ከእነኝህ በተጨማሪ በሕግ ጉዳያቸው እየታየ የሚገኝም አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ ኦፊሰሮቻችሁን የሥራ ላይ ሥነምግባር የምትከታተሉበት አካሄድ አላችሁ? ከሆነስ በከተማዋ የደንብ ጥሰቶች ለምን ተበራከቱ የሚለውን ጉዳይ ገምግማችሁ ለይታችኋል?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** በከተማ ውስጥ የደንብ ጥሰቶች ለምን ይበዛሉ? የሚለውን በየጊዜው ይገመገማል። ሳይገመገም የታለፈበት ጊዜ የለም። ለምን ይበዛሉ? ለሚለው መልሱ ከተማ ስለሆነ ነው። ነገር ግን ይህን ችግር ለመቀልበስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብረን እየሰራን እንገኛለን።

የአፊሰሮቻንን እና አመራሮችን የሥነ ምግባር ሁኔታ የምንከታተልበት የዲሲፕሊን ኮሚቴ በየደረጃው አለ። የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ዳይሬክተርም አለ። ይህ ዳይሬክተር በወረዳ እና በክፍለ ከተማ የራሱን ፈጻሚ አካል በማደራጀት ከሕዝብ ከሚሰጡ ጥቆማዎች በመነሳት እና ራሱም በሚያደርገው ክትትል የሕግ ጥሰት በፈጸሙ አፊሰሮች ላይ እርምጃ ይወሰዳል።

**አዲስ ዘመን ፡- በከተማዋ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ከሕዝብ ጋር ተባብሮ እና ተናብቦ የመስራቱ ነገር ምን ይመስላል ?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** ከዚህ በፊት ተቋሙ ከኅብረተሰቡ ጋር ግንኙነት ከማድረግ ጋር ክፍተቶች ይታዩበት ነበር። በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት ከተቀረፉ ችግሮች መካከል አንዱ ከኅብረተሰብ ጋር ተባብሮ ችግሮችን የመፍታት አሰራሩን በስፋት ማከናወን ነው። በወረዳ ደረጃ በ120 ወረዳዎች ለሁለት ጊዜያት ከኅብረተሰቡ ጋር ተገናኝተናል።

የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ኅብረተሰቡ በሚኖርበት ወረዳዎች ወርዶ ችግሮችን መፍታት እና በጋራ ለመስራት ውይይት አድርጓል። በክፍለ ከተማ እና በከተማ ደረጃ ከማኅበረሰቡ ጋር በርካታ ውይይቶች ተደርገዋል። እነኚህ የሕዝብ ውይይቶች በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረን አስችለዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ፍራፍሬ እና መድኃኒት የመሰሉ በቀላሉ የሚበላሹ ንብረቶች በሚወረሱ ጊዜ እንዴት ታስቀምጣላችሁ? እንዴትስ ታስወግዳላችሁ?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** እንደ ፍራፍሬ ዓይነት ንብረቶች ከመወረሳቸው በፊት ቢቻል ቢቻል በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ላይ እንዳይሳተፉ ምክር ተሰጥቷቸው የሚለቀቁ አሉ። ነገር ግን የተደረገውን ምክር ተላልፈው በሕገወጥነት የሚቀጥሉ ከሆኑ እንዲወረሱ ይደረጋል። ለጨረታም ቀርቦ ይሸጣል። መድኃኒትን በተመለከተ መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚያስወግድበት አሰራር አለ።

**አዲስ ዘመን ፡- ከጸጥታ ጋር ተያይዞ የሚሰሩ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት አሉ። ከዚህ አንጻር የደንብ ማስከበር ምን ያደርጋል የሚሉ ሰዎች አሉ። ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ አንጻር ይህን የሰዎች አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?**

**ሻለቃ ዘሪሁን፡-** የደንብ ማስከበር ከተቋቋመለት ዓላማ አንጻር የፌዴራል ፖሊስን ወይም የአዲስ አበባ ፖሊስን ተክቶ የሚሠራ ተቋም አይደለም። ራሱን የቻለ በአዋጅ የተሰጡት ኃላፊነቶች አሉት። ነገር ግን የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ከጸጥታ ችግር ጋር የሚታዩ ችግሮችን ከተለያዩ የጸጥታ አካላት ጋር በመሆን ችግሮችን ለማስወገድ ሥራዎችን ይሠራል።

**አዲስ ዘመን ፡- ለቃለ ምልልስ ስለተባበሩን እናመሰግናለን።**

**ሻለቃ ዘሪሁን ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ሆስፒታሉ በሚሰጠው አገልግሎት ህብረተሰቡን ደስተኛም፤ አጋዥም ማድረግ ችሏል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ሆስፒታሉ በሚሰጠው የተቀላጠፈ አገልግሎት ህብረተሰቡን ደስተኛም አጋዥም ማድረግ መቻሉን የወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አስታወቀ:: ሆስፒታሉ በ2013 ዓ.ም በአገልግሎት አሰጣጡ ከጤና ሚኒስቴርም ከክልል ጤና ቢሮም ተሸላሚ መሆኑ ተገልጿል::

የወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ካሊድ ሸሪፋ ጳጉሜን 1 የአገልግሎት ቀንን አስመልክቶ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት ፤ ሆስፒታሉ ህመም አጋጥሟቸው የሚመጡ ተገልጋዮች አስፈላጊውን ህክምና ሁሉ በተቀላጠፈ መልኩ እንዲያገኙ ባለው አቅም ሁሉ እየሠራ ይገኛል::

ቀደም ሲል በአካባቢው በቅርብ የሚገኝ ሆስፒታል ባለመኖሩ በወሊድ ጊዜ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል እናቶች እና ሕጻናት ለሞት ይዳረጉ እንደነበር የቅርብ



**ዶክተር ካሊድ ሸሪፋ**

ጊዜ ትውስታ ነው ያሉት ዶክተር ካሊድ፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ህብረተሰቡ ከራሱ ኪስ አዋጥቶ ሆስፒታሉን ገንብቷል:: ለዚህ አበርክቶውም ህብረተሰቡ በሆስፒታሉ ሊያገኝ የሚገባውን ሁሉ አግኝቶ እንዲሄድ ከሠራተኞች እስከ ሥራ ኃላፊዎች ድረስ ህዝቡን ለማገልገል እየተጉ ይገኛሉ ብለዋል::

ሆስፒታሉ እንደ ሀገር አሉ የሚባሉ የስፔሻሊቲና የሰብ ሸፔሻሊቲ የህክምና አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ እየሰጠ እንደሚገኝ አመልክተው፤ በዚህም በሆስፒታሉ አገልግሎት ፈልገው በሽታቸው ከአቅም በላይ ሆኖ ወደ ሌላ ሆስፒታል ሪፈር የሚደረጉ የታካሚዎች ቁጥር ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ ያነሰ መሆኑን ገልጸዋል::

በሆስፒታሉ አገልግሎት አሰጣጥ ህብረተሰቡ ደስተኛም አጋዥም መሆኑ በየጊዜው በምንሰራው ጥናት አረጋግጠናል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ከዚህ በጨማሪም በ2013 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሆስፒታሎች በተደረገ ውድድር የወራቤ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አንደኛ ሆኖ ተመርጦ እንደነበር ሥራ አስኪያጁ አስታውሰዋል::

ዶክተር ካሊድ ለዚህ ውጤት ዋናው ምክንያትም የሆስፒታሉ ሠራተኞች አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣ ሰው አገልግሎቱን ማግኘት አለበት የሚልና ሥራን ማሳደር ተገቢ አይደለም የሚሉ መርሆች የሚከተሉ በመሆናቸው ነው ብለዋል::

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በሆስፒታሉ ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ስፔሻላይዝድ ሀኪሞች፣ በብዙ ሆስፒታሎች የማይገኙ የህክምና መሳሪያዎች፣ የላብራቶሪ ግብዓቶች ፣ የመድሃኒት አቅርቦቶችና ትላልቅ የህክምና ማሽኖችን አሟልቷል:: በቀጣይም እነዚህን የህክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶች በአግባቡ በመጠቀም ለታካሚው ህብረተሰብ ተገቢውና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንደሚሰጡ ቃል ገብተዋል::

ዶክተር ካሊድ ሆስፒታሉ ጤና ሚኒስቴር የሚያወጣቸው ፕሮጀክቶችን የሚተገብርና በተለየ መልኩ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለይቶ ለህብረተሰቡ እየሰራ በመሆኑ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን አትርፏል ነው ያሉት::

ሥራ አስኪያጁ ህብረተሰቡ እንዳይኑ ብሌን በሚያየው ሆስፒታል የሚፈልገውን አገልግሎት አግኝቶ እንዲሄድ በቀጣይም በትጋት መስራታቸውን እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል::

## “አገልጋይነት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጥረት በፈጣሪም ሆነ በሰዎች ዘንድ ዋጋ የሚያስጥ ተግባር ነው፤ ይህን ተግባርን ይበልጥ ማጠናከር ይገባል።

እንደ ዶክተር ሊያ ገለጻ፤ አገልጋይነት የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ ከራስ በማስቀደም ሊሳተፉበት የሚገባ በጎ ተግባር ነው።

ቅን አገልጋይ ያለውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ጊዜና ጉልበት ያለመሰሰት የሚሰጥ መሆኑን ጠቁመው፤ በአገልጋይነት ውስጥ ሀገር የምታተርፈውን በመገንዘብ ይበልጥ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

የጤና ባለሙያዎች ከራሳቸው በፊት ተገልጋዮችን በማስቀደም አገልግለዋል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ የዜጎችን የጤና ችግር ለመቅረፍ ባልተመቸ ሁኔታ ውስጥ እየሰሩ መሆኑን አንስተዋል።

የጤና ባለሙያዎች ዜጎች በኮቪድ ወረርሽኝ፣ በጦርነትና በተፈጥሮ እንዲሁም በሰው ሰራሽ አደጋዎች ወቅት ከፊት ቀድመው ሕዝብን የሚያገለግሉ ብርቱ ሠራተኞች መሆናቸውን አመላክተዋል።

መልካም አገልጋይ ለመሆንና ችግርን ለመፍታት ለጋስነት ወይም ሰጪነትን ይፈልጋል ያሉት ሚኒስትሯ ባልተመቸ ሁኔታ ውስጥ መፈጸም የሚያስችል መሰጠትን የሚፈልግ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

ከጤና ኤክስቴንሽን ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ባለሙያዎች የተገልጋያቸውን ጤና ለመጠበቅ አገልግለዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በቅንነት እራስን ሰጥቶ በማገልገል የሚጎዳ ሰው የለም ያሉት ሚኒስትሯ፤ ማገልገልን የሁል ጊዜ ልምድ በማድረግ ለማህበረሰብ ለውጥ መሥራት ይገባል ብለዋል።

አገልጋይነት በጤናው ዘርፍ ሕክምና ተኮር አገልግሎት መስጠት መሆኑን ጠቅሰው፤ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አገልጋይነት ለሀገራዊ ሁለንተናዊ ዕድገት መሠረታዊ ተግባር ነው፡፡

መልካም አገልግሎት ከአሃዝ ውጪ በስሜት የሚገለጽ ትልቅ ፍቅር አለው ያሉት ዶክተር መኩሪያ፤ ተገልጋዩን ማክበር፣ ችግሩን መረዳትን ጨምሮ መቅረፍ የአገልጋይነት ስሜቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ለተገልጋዩ የሚገባውን ክብር መስጠትና ችግሮችን በመካፈል መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በመድረኩ የመወያያ ጽሁፍ ካቀረቡት መካከል የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፣ የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር)፣ የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሮሁል ሀሰን ይገኙበታል።

## አገልጋይነት ያለንን ጊዜና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ቆይታ እንደገለጹት፤ ወደ መንግሥት ኃላፊነት የሚመጣ ሰው ለማገልገል የቆረጠ መሆን አለበት እንጂ በአንድ ጊዜ ሁለት አይነት ሰው መሆን፤ በአንድ በኩል አገልጋይ፣ በሌላ በኩል ነጋዴ ወይም ሀብታም ሆኖ መቀጠል አይችልም ብለዋል::

ኃላፊነት በተረከቡ ማግስት ከአመራሩ ጋር በመነጋገር 24 ሰዓት፣ ሰባቱንም ቀናት ማገልገል ይገባል የሚል መተማመን መፍጠር መቻሉንም ነው የተናገሩት::

እሁዳችን አገልግሎት ነው፣ ቅዳሜያችን አገልግሎት ነው፣ ማለዳችን አገልግሎት ነው፣ ምሽታችን አገልግሎት ነው፣ ቀናችን አገልግሎት ነው ሲሉም ነው ከንቲባ አዳነች የተናገሩት::

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በደከመና በተሰላቸ ሠዓት በቅንነት ለማገልገል ስለማይቻል ኃላፊነትን መልቀቅ ይገባል:: አገልግሎት ውስጥ ልግመኝነት፣ ሌብነት እና ሌሎች ነገሮች ደባል ሆነው ከመጡ ትክክለኛ አገልጋይ መሆን አይቻልም::

‹‹አገልግሎት ከግል ፍላጎት በላይ ነው:: እኔ በዚህ አምናለሁ፤ እየኖርኩበትም ነው ብዬ ራሴን በዚህ ደረጃ መግለጽ እችላለሁ›› ብለዋል::

አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ የከተማ አቀፍ ሚና ያላት እና ለኑሮ ምቹ ማድረግ እንደሚገባ በመጠቆምም፤ የኢትዮጵያ ምልክት፣ የአፍሪካ መልክ ያላት፣ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ሚናዋን በሚገባ የምትወጣ፤ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማቅረብ የምትችል ለማድረግ መነሻ ሃሳብ ተይዞ ወደ ሥራ መገባቱንም ጠቁመዋል::

የአዲስ አበባ ሕዝብ የተለያየ የገቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያስታወሱት ከንቲባዋ፤ ሁሉንም ማገልገል አለብን፣ ዝቅተኛ ገቢና ምንም ገቢ የሌላቸውን የከተማ ነዋሪዎችንም አገልግሎት በትክክል የሚደርሳቸው፣ የሚታሰብላቸው ማድረግ አለብን ብለዋል::

የሰው ተኮር ሥራ ዓላማ የተቸገሩ ነዋሪዎች ከገቢ የሚካፈሉ፣ ከልማቱ የሚቋደሱ ማድረግ ነው:: ፍትሐዊነት የነገሠባት ከተማ ማድረግ አለብን፤ ከምንሠራቸው ሥራዎች በፊት ሰው እናስቀድማለን ሲሉም ገልጸዋል።

ሰው ላይ ያልዋለ፤ ለሰው ሕይወት የማይደርስ የአዲስ አበባ በጀት በፍትሐዊነት ለነዋሪው ደርሷል እንደማይባልም አመልክተዋል::

ለዚህም “መጀመሪያ የአዲስ አበባ ሕጻናት፤ ነገ ይህችን ሀገርና ከተማ ተረክበው የሚያሳድጉ ልጆች እየተራቡ ትምህርት ቤት ውስጥ መዋል የለባቸውም”



**አዳነች አቤቤ**

ብለን የተነሳነው አንድ ማሳያ ነው ብለዋል::

ልጆች ተርበው ሲወድቁ ከማየት በላይ ህመም የለም ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በተለይ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን ለመመገብ ከተማ አስተዳደሩ ወስኖ የተማሪዎች ምገባ መጀመሩን አስታውሰዋል::

ትግበራው ሲጀመር ምገባ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር ወደ መቶ ሺህ ነበር። ከአንድና ከሁለት ዓመት በኋላ ሶስት መቶ ሺህ መድረስ ተቻለ:: በ2015 ዓ.ም 750 ሺ ተማሪዎችን በቀን ሁለት ጊዜ እንመግባለንም ሲሉ ተናግረዋል::

በተጨማሪም ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ዩኒፎርም፣ ደብተር፣ እስኪሪብቶና መሠረታዊ ግብዓቶች እንደሚቀርብላቸው፣ ከ20ሺ በላይ እናቶች ሥራ አግኝተው ልጆቻቸውን እየመገቡ፣ በእናትነት ፍቅር እየተንከባከቡ እንደሚያገለግሏቸው፣ ተማሪዎች በእኩልነት አብረው እንደሚጫወቱ፤ ትምህርታቸው ላይ ትኩረት አድርገው እንደሚማሩና የወላጆችም ጫና በዛው ልክ መቀነሱንም ጠቁመዋል::

ሀገር አገልግለው በተለያየ ምክንያት የኑሮ ዕክል ገጥሟቸው ለችግር የተጋለጡ ብዙ ወገኖች አሉ:: እነዚህ ወገኖች ልንመለከታቸው ይገባል:: መንግሥት ብቻውን ሰርቶ እነዚህን ማኅበራዊ ጫናዎች ስለማይቀንስ በባለሀብቱና ነዋሪው በትብብር 19 የምገባ ማዕከላት ተገንብተዋል::

ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ወንዝ ዳር የሚገኙ የፈራረሱ የቀበሌ ቤቶች ውስጥ ለሚኖሩ እናቶችና አባቶችን 21 ሺ ቤቶችን መሠራታቸውንም አስታውሰዋል:: በእርጅና ዘመናቸው አረፍ ብለው ሀገርንና ትውልዱን እየባረኩ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር መቻሉንም አመልክተዋል::

እስከ 2011 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ዳቦ የማምረት አቅም ከ300 ሺህ የማይበልጥ እንደነበር ያስታወሱት ከንቲባ አዳነች፤ 27 አዳዲስ የዳቦ ፋብሪካዎች መገንባታቸውንና በቀን ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዳቦ የማምረት አቅም ላይ መደረሱንም አመልክተዋል::

ሰው ተኮር በምንለው የልማት ሥራችን ለሰው በመድረስ፤ ተመግቦ እንዲያድር፤ ደስ ብሎት እኩልነትና ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ እንደ ዜጋ ተገቢውን ክብርና ፍቅር የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተችሏል::

የኮሮና ቫይረስ ሀገራችን ላይ ስጋት በደቀነበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያውያን ያቀረቡትን “ማዕድ አጋሩ” ጥሪ ተከትሎ የተጀመረው ማዕድ ማጋራት አዲስ አበባ ባህል አድርጋዋለች ብለዋል:: ለዚሁ ተግባር በየዓመቱ ከሦስት ቢሊዮን ብር ያላነሰ እንደሚሰበሰብ፣ በየዓመቱ በሚኖሩ በዓላት ከ600 ሺ በላይ ዜጎች ማዕድ እንደሚጋሩም ጠቁመዋል::

ይህ ቁጥር በድግግሞሽ ሲታይ በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋን ማገልገል ተችሏል:: ሰው ካለው ነገር ላይ በማካፈል ጎረቤቱን መርዳት እንዲችል ተሠርቷል ብለዋል::

እዚህም እዛም የሚጣሉ ሕጻናትንም በፍጥነት ወደ ሕጻናት ማሳደጊያ ክፍል እንወስዳለን:: የከተማዋን ነዋሪና ባለሀብቱን በማሳመን ከቻሉ ልጆቻቸው አድርገው ወስደው እንዲሳድጓቸው፣ ያ የሚከብዳቸው ከሆነ ደግሞ በሕጻናት ማቆያዎቻችን ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ እንዲሸፍኑ በማድረግ ለሕጻናትም የተሻለ ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል::

# ንግድና ግብይት

# አቅርቦትን በማስፋትና ህገወጥነትን በመቆጣጠር

## የኑሮ ውድነትን የማረጋጋት ስራ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ዓለም አቀፋዊና አገራዊ በሆኑ በርካታ ምክንያቶች የተነሳ በኢትዮጵያ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት የሸማቹን አቅም በእጅጉ እየተፈታተነው ይገኛል። መንግሥት ይህን መሰረታዊ ችግር ለመፍታት የተለያዩ መንገዶችን ቀይሶ መስራቱን አጠናክሮ ቀጥሏል። ለእዚህም የኑሮ ውድነቱን ሊያረግቡ የሚችሉ የተለያዩ አማራጮች መንገዶችን እየተጠቀመ ነው።

በተለይም በበዓላት ወቅት ካለው ከፍተኛ የሸቀጦች ፍላጎት ጋር ተያይዞ የምርት እጥረት እንዳይከሰት እንዲሁም ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ግሽበት እንዳይፈጠር ለማድረግ ገበያን የማረጋጋት ሥራውን አጠናክሯል። በአሁኑ ወቅትም መጣሁ መጣሁ ከሚለው የአዲስ ዓመት በዓል አስቀድሞ የበዓል ገበያውን ለማረጋጋት እየሰራ ነው። ለእዚህም የምርት እጥረት እንዳይከሰትና ህገወጥነትን ለመቆጣጠር ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

ሰሞኑን የበዓል ገበያው እንደሚደራ ይታወቃል። ለዚህም በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ከነሐሴ 27 ቀን 2015 ጀምሮ እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ የሚቆይ የባዛር ገበያ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲኖር አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ባለፈው ሳምንት ማስታወቁ ይታወሳል። ቢሮው ገበያው እንደሚኖር ከመግለጽ ባለፈ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት እየሠራ ስለመሆኑም ነው ያስታወቀው።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንም እንዲሁ በመላው ኢትጵያውያን ዘንድ በድምቀት የሚከበረውን የዘመን መለወጫ በዓል ምክንያት በማድረግ የዋጋ ንረት እንዳይከሰትና በቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ አብረው እየሠሩ መሆናቸውን በቅርቡ በጋራ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። ተቋማቱ በመግለጫው እንደጠቀሱትም፤ ከበዓሉ ጋር በማያያዝ አንዳንድ ወገኖች ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዳያደርጉና የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ እንዳይባበስ፤ የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ለማድረግ ይሰራሉ፤ የገበያ ቁጥጥርና ክትትልም ያደርጋሉ።

ለእዚህም የቅድመ ዝግጅት ተግባሮች መከናወናቸውን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ አስታውቀዋል። ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ በአገሪቱ የኑሮ ውድነት ስለመኖሩ መንግሥት ይገነዘባል፤ የኑሮ ውድነቱ መነሻ ምክንያቶች ውስጣዊና ውጫዊ ናቸው። ለዘመን መለወጫ በዓል የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይገጥም በቂ ዝግጅት ተደርጓል።

ሚኒስትር ዴኤታው ውስጣዊ ምክንያቶች ተብለው በዋናነት ከተለዩት መካከል ካለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ጋር ተያይዞ የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን አንዱ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ያለውን ምርት ለማቅረብም በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ችግር እንቅፋት መፍጠሩን ጠቁመዋል። ይህም ሸቀጦችን በተፈለገው ጊዜና መጠን ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር ማድረጉን ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም በተወሰኑ ክልሎች በነበረው የኬላ መዘጋት ምርትን ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር አስቻይ ሁኔታ እንዳልነበር አስታውሰው፣ ይህም የምርት እጥረት እንዲከሰት አርጎ እንደነበር ገልጸዋል። ይህን ችግር መቆጣጠር መቻሉን ነው የገለጹት።

ዓለም አቀፉ ሁኔታም ለኑሮ ውድነቱ መንስኤ መሆኑን ያነሱት አቶ ተሻለ፤ ለአብነትም የዩክሬንና የሩስያ ጦርነት በምርቶች ዋጋ ላይ ጭማሪ ማስከተሉን አመልክተዋል። ኢትዮጵያ የምግብ ሸቀጦችን ጨምሮ በርካታ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከውጭ የምታስገባ መሆኑ የኑሮ ውድነቱን ዓለማቀፋዊ ጫናም ያለው እንዳረገው ተናግረዋል። እንደ ስኳር፣ ዘይት፣ ሩዝ፣ የህጻናት ወተትና የመሳሰሉት ከውጭ ተገዝተው የሚገቡ በመሆናቸው የዋጋ ንረቱ ዓለማቀፋዊ ግሽበትን በማስከተል የኑሮ ውድነቱን ከፍ እንዲል አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አቶ ተሻለ እንደተናገሩት፤ መንግሥት የዋጋ ንረቱን ለመከላከልና ገበያውን ለማረጋጋት የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል። በተለይም ባለፉት ሶስት ወራት በበላይ አመራር የሚመራ ሥራ ለማከናወን ተሞክሯል። ከእነዚህም መካከል የሰንበት ገበያ አንዱ ሲሆን፤ ይህም በየከተሞቹ ተግባራዊ ተደርጎ ሸማቹ በቀጥታ ምርቶችን ከአምራቹ በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችል ተደርጓል።



አቶ ተሻለ በልሁ



አቶ ቀጸላ ሸዋረጋ

የሰንበት ገበያ በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያለውን ርዝመት ማሳጠር ማስቻሉን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በዚህም አላስፈላጊ የሆኑና ምንም እሴት ሳይጨምሩ ትርፍ ይሰበስቡ የነበሩ አካላትን ከንግድ ሰንሰለት ውስጥ ማስወጣት ተችሏል ብለዋል። በተለይም በእህል ንግድ፣ በቁም እንስሳትና በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ ድለላን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ማስቀረት የተቻለበት ነበር ሲሉ ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ተሻለ ገለጻ፤ ህገወጥ ንግድን ለመቆጣጠር የሚያስችል ህጋዊ እርምጃ ተወስዷል። በዚህም ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ 395 ሺህ በሚጠጉ ህገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ገበያውን ማረጋጋትና ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪን መቆጣጠር ተችሏል።

መጪው የዘመን መለወጫ በዓልን አስመልክቶ በሸቀጦች ላይ የዋጋ ንረት እንዳይከሰት በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል። በአገሪቱ ካሉት ከተሞች በዋናነት ከፍተኛ ፍላጎትና ብዙ ሸማች ያለው አዲስ አበባ ከተማ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ለዚሁ ገበያ የሚመጥን ምርት ለማቅረብ እየተሰራ ነው ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ 170 በሚጠጉ የእሁድ ገበያዎች ለበዓሉ አስፈላጊ የተባሉ የምርት አይነቶችን በስፋት ለማቅረብ ከህብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር እየተሠራ መሆኑንም ነው አቶ ተሻለ የተናገሩት። ከሕብረት ሥራ ማሕበራቱ ጋር ኮንትራት በመፈራረም ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ እንደ ሽንኩርት፣ የቁም እንስሳትና ሌሎች የምርት አይነቶችን ለተጠቃሚው ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል። በተለይም በከተማ የተደራጁ የሸማች ሕብረት ሥራ ማሕበራት የገንዘብ እጥረት እንዳያጋጥማቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ብድር በማመቻቸት ምርቶቹን እንዲያቀርቡ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ሲሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የኦሮሚያ ክልል በበኩሉ ስድስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት በማድረግ ምርቶች በስፋት እንዲቀርቡ ተደርጓል። ሌሎችም ክልሎች እንደየአቅማቸው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ብድር በማቅረብ የፋይናንስ እጥረት እንዳይጋጥምና ምርቶችን በበቂ መጠንና በወቅቱ ማቅረብ እንዲቻል ተሰርቷል።

በመንግሥት ደረጃ ዘይትን በተመለከተ ሰፊ አቅርቦት መኖሩን አቶ ተሻለ ጠቅሰው፤ አሁን ገበያ ላይ ካለው ዋጋ በላይ ዋጋው ሊያሻቅብ የሚችልበት ምንም

> **በዓሉን ምክንያት በማድረግ ገበያን ለማረጋጋት የሚሠራው ሥራ እንዳይደናቀፍ በየቦታው ግብረኃይል ተቋቁሟል፤ ከፌዴራል እስከ ታችኛው የመንግሥት መዋቅር ወረዳ ድረስ እየተሰራ ነው። በተለይም የፖለቲካው አመራሩ እዚህ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት ግዴታው ነው**

ዕድል እንደሌለው ነው የገለጹት። ስለሆነም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት በሌለው ሁኔታ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ እንደማይኖር ተናግረው፣ በህገወጥ መንገድ የሚፈጠር የዋጋ ጭማሪ ካጋጠመም ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ተገቢው የሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወስድም አስገንዝበዋል።

የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል ዘላቂው መፍትሔ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሆነ የገለጹት አቶ ተሻለ፤ በአሁኑ ወቅት በክልሎች ጭምር ተግባራዊ እየሆነ ያለው የሌማት ትሩፋት ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ተናግረዋል። ለአብነትም በአሁኑ ወቅት ከሶማሌ ክልል የሽንኩርት ምርት እየገባ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በአዲስ አበባ ከተማም የሌማት ትሩፋትን ዕውን ለማድረግ በተደረገው ጥረት በሚሊዮኖች የሚቆጠር እንቁላል ማምረት ተችሏል። ይህ ደግሞ ገበያውን ማረጋጋት እንደሚቻል መሰረት ሆኗል። እንቁላል ከአስር ብር በታች ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል። ዶሮ፣ በግና ፍየልም እንዲሁ ለማቅረብ የአዲስ አበባ መስተዳደርና ክልሎች ዝግጅት አድርገዋል።

በዓሉን ምክንያት በማድረግ ገበያን ለማረጋጋት የሚሠራው ሥራ እንዳይደናቀፍ በየቦታው ግብረኃይል መቋቋሙን የጠቀሱት አቶ ተሻለ፤ ከፌዴራል እስከ ታችኛው የመንግሥት መዋቅር ወረዳ ድረስ እየተሰራ ነው ብለዋል። በተለይም የፖለቲካው አመራሩ እዚህ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት ግዴታው እንደሆነ በመጥቀስ፤ የፖለቲካ አመራሩ ህብረተሰቡን መታደግ የሚችልበትን የመጨረሻ አቅም ተጠቅሞ እንዲሠራ አቅጣጫ በመስጠት በተቀናጀ መንገድ እየተሠራ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

ከዚህ አልፎ ዋጋን ለማናር የሚደረግ ጥረት ካለ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቀዋል። መሰረታዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያት በሌለበት በዓልን ተገን በማድረግ ዋጋን አንራለሁ የሚል ስግብግብ ነጋዴ ሲያጋጥም ማህበረሰቡ ጥቆማ በመስጠት ሊተባበር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የምርት እጥረት ባለበት ጤናማ የሆነ የንግድ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል ገልጸው፣ የንግድ ሥርዓት በውድድር እንዲመራ ማድረግ ለኑሮ ውድነቱ ዘላቂ መፍትሔ እንደሚሆን አቶ ተሻለ ጠቁመዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ምርት እንደልብ ተመርቶ ወደ ገበያው መግባት አለበት። ይህ ሲሆን አንዱ ነጋዴ ከሌላው ነጋዴ በውድድር ያቀርባል። የግብርና ምርቶች በስፋት ወደ ገበያው ሲገቡ ተመጣጣኝ ዋጋ ይፈጠራል። በተመሳሳይ አቅርቦት ሲያጥር ውድነቱ በዛ ልክ ይቀጥላል። ስለዚህ ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማምጣት የምርት አቅርቦትን ማስፋት የግድ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንም በአሉን አስመልክቶ በሸቀጦች አቅርቦት በኩል ከፍተኛ ዝግጅት ማድረጉን የኮርፖሬሽኑ የኦፕሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ቀጸላ ሸዋረጋ አስታውቀዋል። በዓል ሲመጣ የሸማቹ ፍላጎት እንደሚጨምር ጠቅሰው፣ የንግዱ ማህበረሰብ ደግሞ ይህንኑ ፍላጎት ተገን በማድረግ የሚያደርገውን የዋጋ ንረት ለመከላከል እንዲሁም ህብረተሰቡን ካልተፈለገ የዋጋ ንረት ለመታደግ ኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለአዲስ ዓመት በዓል የፓልም ዘይት በከፍተኛ መጠን ለአዲስ አበባ እንዲሁም ለክልል ከተሞች በቀድሞ ዋጋ እንዲከፋፈል እየተሰራጨ ነው። ዘይቱ በበቂ መጠን የገባ ሲሆን፤ በኢንዱስትሪ ግብዓት ልማት ድርጅት በኩል እየተሰራጨ ይገኛል። ዋጋውም አዲስ አበባ ላይ ባለ ሶስት ሊትሩ 324 ብር፣ ባለ አምስት ሊትሩ 526 ብር እና ባለ 20 ሊትሩ 2064 ብር እየተሸጠ ነው። የዘይቱ አቅርቦት እስከ መስቀል በዓል ድረስ ያለ እጥረትና የዋጋ ጭማሪ የሚቀጥል ይሆናል።

ለክልሎችም እንዲሁ የዘይት ምርትን ጨምሮ የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች በስፋት እየቀረቡ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ቀጻላ፤ በየክልሉ ምን ያህል መጠን ተደራሽ መሆን እንዳለበት ተደልድሎ እየተሰራጨ መሆኑን ተናግረዋል።

ከምግብ ሸቀጣሸቀጦች በተጨማሪ ከአዲስ ዓመት ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ሸቀጥ የትምህርት ቁሳቁስ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ከትምህርት ቁሳቁስ መካከልም አንዱ የሆነውን ደብተር ለሕብረተሰቡ ለማቅረብ ዝግጅቱ መጠናቀቁን አቶ ቀጻላ ይገልጻሉ።

ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚው ኮርፖሬሽን ደብተር ለማቅረብ እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል። በአሁኑ ወቅት ደብተር ገበያ ላይ በከፍተኛ ዋጋ እየተሸጠ ይገኛል ያሉት አቶ ቀጻላ፣ በዚህም ህብረተሰቡ እየተቸገረ መሆኑን መንግሥት መገንዘቡን ገልጸዋል። ይህን ችግር ለመፍታትም ደብተር ከቻይና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገባ ተደርጓል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በእርግጥ ችግሩ በዓለም ካለው የወረቀት ዋጋ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። ስለዚህም ለኑሮ ወድነቱ አባባሽ ምክንያት ነውና መንግስት ይህን ችግር ለመፍታት አስቀድሞ እየሰራ ይገኛል። ጥራቱን የጠበቀ ደብተርም ከቻይና እንዲገባ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ምርቱ እየተጓጓዘ ነው። በቅርቡ ገበያ ውስጥ እንደሚገባ ይደረጋል። ደብተሩ ከኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት ጋር በመነጋገር በቅርቡ እንደሚደርስና በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ይቀርባል።

በሌሎች ሸቀጦች ላይም በቂ ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰው፤ በዓሉን አስመልክቶ የሚኖር ምንም አይነት ጭማሪ አለመኖሩን አስረድተዋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

## አገልጋይነት ሥልጣኔ ነው

**ዋስልኝ አየለ**

ሥልጣኔ የሚለው ቃል የሰለጠኑ ናቸው ከሚባሉት የአውሮፓ አገራት የመጣ የሚመስለው ይኖር ይሆናል፡፡ ይህ ቃል ግን በልማድ ፈረንጅ የምንለው (ነጭ) የሚባል የአውሮፓ ዜጋ እስከመኖሩም በማያውቀው የአገራችን ሕዝብ ውስጥ ይታወቃል፡፡ ‹‹የእገሌ ልጅ ሥልጡን ነው፣ እገሌ ሥልጡን ነው…›› ሲሉ እንሰማለን፡፡ ሥልጡን ማለት በስነ ምግባር የታነፀ፣ ትሁት የሆነ ማለት ነው።

በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ይህ ከሆነ፤ እነዚህ ሥልጡን የሚሏቸው ሰዎች (ልጆች) ድርጊታቸው ሲታይ ሰዎችን በትህትና የሚያገለግሉ ናቸው። ለታላላቆቻቸው የሚታዘዙ፣ ትልቅ ሰው ሲመጣ ከመቀመጫቸው የሚነሱ፣ ትልቅ ሰው ሲያዝዛቸው በትህትና ‹‹እሺ›› ብለው የሚሄዱ፣ ዕቃ ወይም የሆነ ሸክም የያዙ አዛውንቶች ሲያገኙ ተቀብለው የሚሸኙ ናቸው፡፡ እነዚህን ሰዎች የአካባቢው ሰው ‹‹ሥልጡን›› ይላቸዋል፡፡ የሰለጠኑ ማለት ነው፡፡

ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ በመጣ ትርጉም ደግሞ መሰልጠን የሚለውን ቃል ማህበረሰቡ ከሰጠው ትርጉም ተቃራኒ የሆነ ትርጉም ሲሰጠው ይታያል፡፡ ይሔውም፤ መሰልጠን ማለት አለባበስ፣ አነጋገርና አንዳንድ ውጫዊ ፋሽኖች ላይ ያተኮረ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በነባሩ የማህበረሰባችን ትርጓሜ ግን መሰልጠን ማለት ሰዎችን ማገልገል ነው፡፡

ዛሬ የአገልጋይነት ቀን ነው ተብሏል፡፡ በዚሁ እግረ መንገድ ስለ አገልጋይነት እንታዘባለን፡፡ አገልጋይነትን ያህል ትልቅ ነገር በብዙ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች እንዴት እንደሚያራክሱት እንታዘ ባለን፡፡

ተቋማት ስማቸው ራሱ ‹‹አገልግሎት ሰጪ ተቋም›› ተብለው ነው የሚገለጹት፡፡ ገላጪ ትርጉም ነው፡፡ እንደየ አይነታቸው ሕዝብ የሚፈልገውን አገልግሎት የሚያገኝበት ማለት ነው፡፡ በእነዚህ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች ደግሞ አገልጋይ ናቸው ማለት ነው፤ ሕዝብን እያገለገሉ ነው። እዚህ ላይ ነው ታዲያ ብዙ ነገሮችን የምንታዘበው፡፡

አንዳንዶቹ አገልጋይነታቸውን ይረሱትና ጌታ ይሆናሉ፡፡ ተገልጋዩ አገልግሎቱን የሚያገኘው በእነርሱ መልካም ፈቃድ ብቻ የሚሆን ይመስላቸዋል፡፡ እርግጥ ነው በአገልጋዩ መልካም ፈቃድ የሚገኙ አገልግሎቶች አሉ፡፡ እነርሱ የበጎ አድራጎት አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው። ኃላፊነት ተወስደው፣ ከሕዝብ በጀት ላይ ደሞዝ የሚከፈለው አገልጋይ ግን በግል በጎ ፈቃዱ ብቻ አይደለም የሚያገለግል፤ በኃላፊነት ጭምር ነው፡፡ ጌታው ሕዝቡ እንጂ እሱ አይደለም፡፡

አገልጋይነት በግለሰቦች ይጀምራል፡፡ ቀደም ሲል እንዳልነው አገልጋይነት ሥልጣኔ እና ጨዋነት ነው። የታነጹ ሰዎች የሚያደርጉት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ባህል በጣም የቆየ እና ልማድ የተደረገ ነው፡፡ ምናልባትም ለየት ከሚያደርጉን በጎ እሳቶች አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ የሰለጠኑ ናቸው በሚባሉት አገራት የምንሰማው አንድ ነውር ነገር አለ፤ ይሄውም በቆዳ ቀለም ሰዎችን መለየት፡፡ በተለይም ጥቁር ነጭን እንደ ጌታ እንዲያይ የሚያደርጉ አመለካከቶች አሉ፡፡ በአውቶብስና በባቡር መጓጓዣዎች ውስጥ ነጭ ቆሞ ጥቁር አይቀመጥም የሚባልበት ሁኔታ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህ የለም፡፡ ትህትና ነው የሚታየው፡፡ በባቡር እና በአውቶብስ ውስጥ ወንበር የሚለቀቀው የቆዳ ቀለም ታይቶ ሳይሆን ሳይንሳዊ መሰረት ያለው ነባራዊ ሁኔታ ታይቶ ነው፡፡ ለምሳሌ በዕድሜ የገፉ አዛውንት ከሆኑ ነው ወንበር የሚለቀቀው፡፡ ይሄ ሳይንሳዊ ምክንያት አለው። በዕድሜ የገፉ ሰዎች ለረጅም ሰዓት መቆየት አይችሉም፤ እየተወዛወዙ መሄድ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል ለነፍሰ ጡር ነው ወንበር የሚለቀቀው፡፡ ነፍሰ ጡር በሆዷ ውስጥ ሌላ ፍጡር አለ፡፡ መቆም ይከብዳታል፣ መወዛወዝ አትችልም፡፡ ስለዚህ በምክንያት ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አክብሮት አለ፡፡ የዕድሜ አቻ ሆነው እንኳን አንተ ተቀመጥ አንተ ተቀመጥ ይገባበዛሉ፡፡ ይህ ትህትና ነው፤ ሥልጡንነት ነው፡፡

ከተማ ቦታ ትራንስፖርት ምቹ ስለሆነ ነገሩን በደንብ ለማጤን አይመች ይሆናል፤ በአገር ቤቱ ልማድ ግን አንድ የማስተውለው ነገር አለ፡፡ እናቶች ወይም አባቶች ሸክም በትከሻቸው ይዘው ሲሄዱ ወጣት የሆነ ሰው ከኋላቸው ከመጣ ማለፍ ነውር ነው፡፡ ሸክሙን ተቀብሎ እስከሚሄዱበት ማድረስ ባይችል እንኳን ትንሽ ያግዛቸዋል። የሚሄዱበት ቅርብ ከሆነ ደግሞ ያደርስላቸዋል፡፡ ከዚያም በአባቶች ወይም እናቶች ይመረቃል፡፡

በተቃራኒው ግን ምንም አይነት ትህትና ሳያሳይ፣ ዘፈን ወይም ፉጨት ነገር እያንጎራጎረ ባላየ ካለፋቸው ‹‹የማነው አሳዳጊ የበደለው!›› ነው የሚሉ፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሚያውቁት ልጅ ማደግ ያለበት በትህትና፣ በጨዋነትና በአገልጋይነት ስለሆነ፡፡ እንዲያውም ለወላጆቹ ሁሉ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ ‹‹ገፍትሮኝ ነው እኮ ያለፈ!›› ይላሉ። ‹‹ገፍትሮኝ›› ሲሉ በእጁ ገፍትሯቸው ሳይሆን ትህትና አለማሳየቱን በግነት ለመግለጽ ነው፤ በእጁ ከመገፍተር አያንስም ለማለት ነው፡፡ አገልጋይነት በዚህ ልክ ነው የኢትዮጵያውያን ልማድ የተደረገው።

የተማረ እና ዘመናዊ በሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ግን አገልጋይነት እምብዛም ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደ መሰልጠን እየተቆጠረ ና፤ መሰልጠን ማለት ግን ሰዋዊ ነገሮችን ማድረግ ነው፡፡ ከሰዋዊ ባህሪያት አንዱ ደግሞ መተሳሰብ ነው፡፡

በጎ ነገር አድርጉ ማለት አስገዳጅ ላይሆን ይችላል፤ ለማገልገል ኃላፊነት ወስደው የተቀመጡት ግን ቢያንስ ለህግና መርህ ተገዢ መሆን አለባቸው። አገርን ማገልገል ኃላፊነት ነው፡፡ የህሊና ብቻ ሳይሆን የህግ ተጠያቂነትም አለበት፡፡ ግለሰቦችንና ማህበረሰብን ማገልገል ደግሞ ተቋማዊ የህግ ተጠያቂነት አለበት፤ በበጎ ፈቃድ ብቻ የሚሆን አይደለም፡፡ ኃላፊነትን በበጎ እና በቅንነት መሥራት ግን የበለጠ ሥልጡን እና ሰዋዊ ያደርጋል፡፡

አገልጋይነት የህሊና ጤና ነው፣ የህሊና ደስታ ነው፣ የህሊና እርካታ ነው፡፡ እኛ ያገለገልነው ሰው ሲያገኝ ማየት ደስ ይላል፤ አለበለዚያ ምቀኝነት ነው የሚሆነው፡፡ በእኛ ስም ሰውን ማስደሰት የህሊና እርካታ ይሰጣል፡፡ በቅንነት በሰራንላቸው ሥራ ሰዎች ያመሰግኑናል፤ መመስገን ደግሞ የሚሰጠውን ደስታ ሁላችንም ቢያንስ በትንሹም ቢሆን አይተነዋል፡፡ በተቃራኒው መወቀስና መረገም ደግሞ ያስጨንቃል፣ ውስጣዊ ነፃነት ያሳጣል፡፡ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል፤ ያ ደግሞ የህሊና መረበሽን ይፈጥራል ማለት ነው፡፡

ለሚለምኑ ሰዎች 100 ብር ብንሰጥ የህሊና ደስታ ነው የሚሰማን፤ ከኪሳችን 10 ብር ቢጠፋ ወይም የታክሲ ረዳት 5 ብር መልስ አልሰጥም ቢለን ግን ለረጅም ደቂቃዎች እንረበሻለን፤ ከረዳቱ ጋር እንጣላለን፤ ከኪሳችን በጠፋች 10 ብር ልንናደድ እንችላለን፤ በበጎ ፈቃድ በሰጠነው 100 ብር ግን ሙሉ ቀን ልንደሰት እንችላለን፤ ምክንያቱም በበጎነት ነው ያደረግነው፡፡ ስለዚህ ሰዎችን ማገልገል የህሊና ደስታን ይፈጥራል፤ በአጠቃላይ አገልጋይነት ሥልጣኔ ነው!

# ዓለም አቀፍ

## ኪም እና ፑቲን ሊገናኙ ነው

የሰሜን ኮሪያው ፕሬዚዳንት ኪም ጆንግ ኡን በዚህ ወር ሩሲያን ሊጎበኙ ነው። ኪም ጆንግ ኡን ወደ ሩሲያ አቅንተው ፑቲንን የሚያገኙበት ዋናው ምክንያት በጦር መሣሪያ ዙሪያ ለመነጋገር እንደሆነ ተዘግቧል።

ሩሲያ በዩክሬን ጦርነት የሚያስፈልጋትን በቂ የጦር መሣሪያ ከሰሜን ኮሪያ እንዲቀርብላት በጽኑ ትፈልጋለች። ሁለቱ ኃያል መሪዎች ተገናኝተው የሚመክሩበት ዋንኛው አጀንዳም ይኸው ሊሆን እንደሚችል ተጠቅሷል። ሁለቱ መሪዎች በትክክል የት እንደሚገናኙ ስፍራው አልተመላከተም።

የኪም እና የፑቲን መገናኘት ጉዳይ መጀመሪያ የተዘገበው በቢቢሲ የሰሜን አሜሪካ አጋር፣ ሲቢኤስ ቴሌቪዥን ሲሆን ይህ ሚዲያ ለመረጃው ምንጭ ያደረገው ደግሞ አንድ የአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣንን ነው። ይህ ዜና ከሩሲያም ሆነ ከሰሜን ኮሪያ በኩል አልተዘገበም።

ሌሎች የዜና ምንጮች ለኒው ዮርክ ታይምስ እንደተናገሩት ደግሞ ኪም ወደ ሩሲያ የሚያጓዙት በጦር ባቡር ሊሆን ይችላል። የጦር ባቡር የሚባለው ጥይት በማይበግረው የብረት ልባስ የተሠራና በርካታ የጦር ቅኝት መሣሪያዎች የተገጠሙለት ልዩ ወታደራዊ ባቡር ነው።

የሁለቱ መሪዎች የመገናኘት ዜና የወጣው አሜሪካ ኪምና ፑቲን በጦር መሣሪያ ዙሪያ እየተነጋገሩ እንደሆነ መረጃ አለኝ ማለቷን ተከትሎ ነው። የአሜሪካ የብሔራዊ ደኅንነት ካውንስል ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ እንደተናገሩት ደግሞ የሩሲያ መከላከያ ሚኒስትር ሰርጌ ሾይጉ ወደ ፒዮንጊያንግ ባቀኑ ጊዜ ኪም ለሩሲያ የጦር መሣሪያ እንድታቀርብ አግባብተዋቸዋል።

ከዚያን ጊዜ ወዲህ ኪምና ፑቲን ትብብራችን እንዴት ይጠናከር በሚለው ዙሪያ በደብዳቤ ሐሳብ ሲለዋወጡ ቆይተዋል። አሜሪካ የሁለቱን መሪዎች ግንኙነት እንዳሳሰባት የገለጸች ሲሆን ሰሜን ኮሪያ መሣሪያ እንዳታቀርብ የተጣለባትን ማዕቀብ እንድታከብር ጠይቃለች።

እንደተፈራው ሰሜን ኮሪያ ለሩሲያ የጦር መሣሪያ የምታቀርብ ከሆነ አሜሪካ ተጨማሪ ማዕቀብ እንደምትጥል የአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት ካውንስል



ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ ተናግረዋል። ኪም እና ፑቲን መገናኘታቸው ያስጨነቃት አሜሪካ ብቻ አይደለችም። ደቡብ ኮሪያም በተመሳሳይ ነገሩ አሳስቧታል።

ሁለቱ አገሮች ከሁሉ ያሳሰባቸው ደግሞ ኪም ለሩሲያ ጦር መሣሪያ ስታቀርብ በምላሹ ሰሜን ኮሪያ ከሞስኮ ምንድነው የምታገኘው የሚለው ነው። የደቡብ ኮሪያ ደኅንነት መሥሪያ ቤት እንደሚጠረጥረው ምናልባት ሦስቱ አገሮች ማለትም ቻይና፣ ሰሜን ኮሪያና ሩሲያ በጋራ የባሕር ኃይል ጦር ልምምድ ለማድረግ የሩሲያው መከላከያ ሚኒስትር ሰርጌ ሾይጉ ሐሳብ ሳያቀርቡ አልቀረም።

ከሁሉም በላይ አሳሳቢ የሆነው ሩሲያ ለሰሜን ኮሪያ በንኩሊየር ጦር መሣሪያ ዙሪያ በዕውቀት ልታግዛት ትችላለች የሚለው ነው። ሌሎች ደግሞ ይህ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ምናልባት ስልታዊ የጦር አጋርነት ግንኙነት ሳይሆን መደበኛ የንግድ ግንኙነት ብቻ ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ።

እነዚህ ተንታኞች እንደሚሉት ሩሲያ ጦር መሣሪያን ተጠምታለች፤ ሰሜን ኮሪያ ደግሞ በቂ የምግብ አቅርቦት የላትም። ስለዚህ ኪም ለሚያቀርቡት የጦር መሣሪያ ከሩሲያ ጠርቀም ያለ ገንዘብ ትከፍላለች ይላሉ። ኪምና ፑቲን በክሬምሊን ወይስ በሌላ ቦታ ይገናኙ የታወቀ ነገር ባይኖርም ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ምንጮቼ ነገሩኝ ብሎ እንደዘገበው ኪምና ፑቲን የሚገናኙት በምሥራቅ ጠረፍ ሩሲያ በምትገኘው ቭላዲቮስቶክ በምትባል የወደብ ከተማ ነው።

ጋዜጣው ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው ከሆነ ከሳምንታት በፊት የሰሜን ኮሪያና የሩሲያ ኃላፊዎች የፕሮቶኮል ጉዳዮችን ለማሰናዳት ወደዚህች የወደብ ከተማ አቅንተው ነበር። አንድ ከዚህ ቀደም በሰሜን ኮሪያ የዩኬ አምባሳደር ሆነው ያገለገሉ ዲፕሎማት ለቢቢሲ ሲናገሩ ኪም ለደኅንነታቸው እጅግ የሚጨነቁ መሪ ከመሆናቸው የተነሳ ምናልባት የሚገናኙበት ቦታ ቀድሞ ከታወቀና በዚህም ስጋትና ጭንቀት ከገባቸው በመጨረሻ ሰዓት ጉብኝታቸውን እስከመሰረዝ የሚደርሱ መሪ ናቸው ብለዋል።

ኪምና ፑቲን ከዚህ ቀደም ሚያዝያ 2019 ዓ/ም በዚህችው አሁን ይገናኙባታል ተብሎ በሚገመተው ቭላዲቮስቶክ ከተማ ተገናኝተው ነበር። ይህን የሆነው ኪም ትራምፕን በቬትናም ካገኟቸውና ከተወያዩ በኋላ ውይይቱ ፍሬ ሳያፈራ መቅረቱን ተከትሎ እንደሆነ ቢቢሲ ዘግቧል።

### ሰሜን ኮሪያ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት መሆኗን በይፋ ያወጀችው የዛሬ ዓመት በመስከረም ወር ነበር

የአገሪቱ መሪ ኪም ጆንግ ኡን ፕዮንግያንግ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት ሆናለች ሲሉ መግለጫቸው የሚታወስ ነው።

ኪም ጆንግ ኡን ውሳኔውን የማይ ቀለበስ ነው፤ ኒውክሌር ካለመታጠቅ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ድርድር ሊኖር አይችልም ሲሉ ለአሜሪካና ለምዕራባውያን መልስ ሰጥተው እንደነበር አይዘነጋም።

ፒዮንግያንግ በተደጋጋሚ ማዕቀብ ቢጣልባትም የኒውክሌር ሙከራዎችን ስታደርግና የኒውክሌር ማብላያዎቿን ስታበለጽግ ነበር።

የሩሲያው መሪና የሰሜን ኮሪያ መሪዎች ሊገናኙ መሆኑ ከተሰማ በኋላ በርካታ የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን ከአሜሪካ ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ ያሉት ሁለቱ አገራት መሪዎች በምን ጉዳይ ላይ ሊወያዩ ይችላሉ የሚለውን ግምታቸውን በማስቀመጥ ላይ ናቸው።

ይሁንና ሁለቱ አገራት በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩረው ሊወያዩ እንደሚችል አጃንስ ፍራንስና የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

# አገልጋይነት - የሕዝብ እርካታ መመዘኛ

በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)

የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ጳጉሜን 1ን የአገልግሎት ቀን ሲል ሰይሟል። ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ያደረገችንን ጳጉሜን ልዩ ልዩ መልዕክት ባላቸው ሕዝባዊ መንፈሶች በማክበር አሳልፈናል። ዘንድሮም በተመሳሳይ ‹የአገልግሎት ቀን› ስንል ጀምረናል።

ጳጉሜን የአዲስ ዓመት መግቢያ በር እንደመሆኗ አዲሱን ዓመት በተለየ መንፈስ ለመቀበልና ከመጠቀም አኳያ አገልጋይነት የሚለው ቃል ጥሩ አድርጎ ይገልጻታል። ባለን ሙያና ኃላፊነት ሀገራችንን እና ሕዝባችንን ከምንጠቅምበት መንገድ አንዱ አገልጋይነት ነው።

አገልጋይነት በብዙ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። የማኅበረሰብን እርካታ መሠረት ያደረገ መንግሥታዊም ሆነ ግለሰባዊ ግልጋሎት አንዱና ዋነኛው መገለጫው ነው፤ ከዚህ በተጓዳኝ ወደአንድነት በሚመሩን የአብሮነት መንፈሶች ውስጥ መገኘትም ሌላው ሀገርን የማገልገያ መንገዳችን ነው።

አገልጋይነት በአንድ ነጠላ እውነት ብቻ የሚቋጭ አይደለም። ከምናስበው ሃሳብ ጀምሮ አገልጋይነትን ማንጸባረቅ እንችላለን። ሃሳባችን አድጎና ጎልቶ ነው በማኅበረሰቡ ውስጥ ተግባር ሆኖ የሚታየው። እናም በጎ ሃሳብ ከማሰብ ጀምሮ የአገልግሎት አድማሳችንን ማስፋት እንችላለን።

የአገልግሎት ቀን መጪውን አስራ ሁለት ወራትና ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናት በሥራ ባህል፣ በሰጥቶ መቀበል ለማሳለፍ እንድንችል የተነሳሽነት መንፈስን የሚፈጥር ነው። እርካታን መሰረት ያደረጉ ውጤት ተኮር ግልጋሎቶች የተነሳሽነት አቅምን ከማጎልበት ባለፈ የሥራ ልምዳችንንም ያነቁታል። በብዙ የምንታማበት የስንፍና ፤ የመጠበቅ አባዜያችንን ያስቀርልናል።

የአገልጋይነት ጽንሰ ሃሳብ በመጠበቅ ወይም ደግሞ ራስን ብቻ ማዕከል አድርጎ በመኖር የሚገለጽ ሳይሆን ሌሎችን እያሰቡና ለሌሎች በመኖር የሚገለጽ ነው። የሀገር እድገትና ብልጽግና ዛሬ ላይ እያገለገልነው ባለው የማኅበረሰብ እርካታ የሚለካ ነው። እርካታ የእድገት መመዘኛ ነው።

ማገልገልና መገልገል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። አንዳቸውን ከአንዳቸው ነጥለን ማየት አንችልም። ስናገለግል ነው የምንገለገለው። ስንሰጥ ነው የምንቀበለው። ሀገር ስንጠቅም ራሳችንን እየጠቀምን ነው። ማኅበረሰብ ስናገለግል ትውልዱን እያገለገልን ነው። ምንም ይሁን አሁን ላይ ለሀገራችን እየሰጠን ያለነው ነገ ላይ እኛ በእጥፍ ከሀገራችን የምንቀበለው ነው።

ብዙ ጊዜ መገልገልን የምንመርጥ ነን። ሀገራችን አገልጋያችን፣ መንግሥት አሳቢያችን እንደሆነ የምናምን ነን። እርግጥ ነው መንግሥት ጠባቂያችን ሀገር ደግሞ መጠለያ ናት። ይሄ እውነት ትርጉም የሚያገኘው ግን እኛ የአገልጋይነት ኃላፊነታችንን ስንወጣ ነው። ኃላፊነታችን ደግሞ ሀገርን በማገልገል የሕዝብን እርካታ ማረጋገጥ ነው።

ዓለም አቀፉ የኢኮኒሚስቶች ማኅበር ሀገርና ማኅበረሰብ የተዋሃዱበትን መነሻ ጽንሰ ሃሳብ ሲተነትን ከሁሉም ልክ ሆኖ ያገኘው እውነት አገልጋይነት የሚለውን ነው። በአገልጋይነት ውስጥ አሁናዊ የማኅበረሰቡን ፍላጎት ከማሟላትና የትውልዱን ጥያቄ ከመመለስ አንጻር ይሄ ነው የማይባል ሚናውን ማየት እንችላለን።

ትላልቅ የስኬት በሮች በማኅበረሰብ እርካታ በኩል የሚከፈቱ ናቸው። እንደሀገር ያስቀመጥናቸው የማደግና የመለወጥ ግቦች አገልጋይነትን ታከው የሚመጡ ናቸው። እውነትና ፍትህን በተጋራ አእምሮና ልብ የምንሠራው፣ የምናስበው ሃሳብና ምግባር ከድህነትና ከኋላቀርነት ሊያወጣን አቅም አለው።

በአዲስ ዓመት መግቢያ በጳጉሜን ደጃፍ ላይ ቆመን በጋራ የምንከብርበትን የአገልጋይነት ቀን፤ ሀገራችንን ብሎም ራሳችንን ከዛም አልፈን ትውልዶችን ተጠቃሚ ለሚያደርገው የአገልጋይነት መንፈስ ራሳችንን የምናነቃቃበትና የምናድስበት ነው።

ሀገራችንን ለማገልገል የሚያንስ እውቀት፣ የሚያንስ ተፈጥሮ የለም። እኛ ሰፊ ሕዝብ፣ ሰፊ መሬት፣ ሰፊ ወጣት፣ ሰፊ ታሪክ ያለን ሕዝብ ነን። ሁሉ ኖሮን አይደለም ለሌላ ለራሳችን መብቃት አልቻልንም። ለዚህ የእኔነት መንፈሶች ተግዳሮቶች ሆነው ይዘውናል። ከእኔነት በጸዳ የአገልጋይነት መንፈስ እስካልመጣን ድረስ ነገም ስንዴ ለማኝ እንደሆንን መቀጠላችን የማይቀር ነው።

ተያይዘንና ተግባብተን በአንድነት መቆም ከቻልን እንደጥንቱ ጊዜ ዓለምን የሚያስገርም ኃይል መፍጠር እንችላለን። ከራሳችን አልፈን በነጻነት አፍሪካን፣ በሰላም ደግሞ ዓለምን አገልግለናል። እነዛን ወንዝ ተሻጋሪ የአገልጋይነት መንፈሶች መልሰን ከድህነት እና ከተረጂነት ለመውጣት ጊዜው አሁን ነው።

ባለን ነገር ሁሉ ሕዝባችንን ማገልገል እንችላለን። በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን የእኛን እርዳታ የምትፈልግበት ጊዜ ላይ ናት። በኑሮ ውድነት፣ በሰላም እጦት በብዙ ማኅበራዊ ቀውሶች ውስጥ ነች። እነኚህ ሀገራዊ ውጥንቅጦች እልባት እንዲያገኙ በአገልጋይነት መንፈስ መታደስ አለብን።

አሁናዊ ችግሮቻችንን ለማሸነፍ ሁሉን አቃፊ የአገልጋይነት ስነልቦና ያስፈልገናል። ሰላምን ሊያመጣ በሚችል፣ አንድነትን ሊፈጥሩ በሚችሉ ሀገራዊ ትብብሮች ላይ በንቃት መሳተፍ አንዱ የአገልጋይነት መገለጫ ነው። ሰላም ስናመጣ፣ ለሰላም ስንለፋ ሀገር አገልግለናል ማለት ነው። ተነጋግረን ስንግባባ፣ ተግባብተን አብረን ስንቆም በሰላም እጦት የሚደርሱ ማኅበራዊ ቀውሶችን ተከላክለናል ማለት ነው።

ሀገር ለማገልገል ካለንበት መጀመር እንችላለን። ምርጡ አገልጋይነት ከቅርብ ጀምሮ ወደሩቅ መሄድ ነው። ከቤት ወደጎረቤት፣ ከጎረቤት ወደአካባቢ ከዛም ወደሀገር። በጽኑ ፍላጎት ውስጥ ከቆምን ሀገር ለማገልገል መንገድ አናጣም። ባለን እውቀት፣ ባለን ጸጋ፣ በተሰማራንበት ዘርፍ በቅንነትና በታማኝነት በመቆም ሀገር ማገልገል እንችላለን። እንዲህ አይነቱ የአገልግሎት መንፈስ ነው በማኅበረሰብ እርካታ ተለክቶ ሀገርን ወደፊት የሚያራምዳት።

ብዙዎቻችን እያወቅን የምንስት ነን። ባለን ኃላፊነት ሀገር ከማገልገል ይልቅ ራሳችንን ወይም ደግሞ ጥቂት በማገልገል የምንደክም ነን። እንዲህ ዓይነቱ ኢ- ፍትሐዊ ግልጋሎት ለሀገር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የለም። አገልጋይነት በእርካታ የሚመዘን የብዙኃኑ ቅቡልነት ነው።

ከሕዝብ ላይ እየሰረቅን፣ በሙስናና በብልሹ አሠራር ተጨማልቀን የምንፈጥራት ኢትዮጵያ የለችም። በእኔነትና በጎጠኝነት ተጠፍረን በግራ እየተቀበልን በቀኝ የምንሰጥ ከሆነ የሀገር ፍቅር አልገባንም። ቢሯችንን ለፀሐፊ ትተን፣ ባለጉዳይ እያጉላላንና በቀን ለሃምሳ ጊዜ የሻይ እረፍት እያልን ሥራ የምንበድል ከሆነ የአገልጋይነት ጽንሰ ሃሳብ ገና አልገባንም። ስልጣንን ተገን አድርገን የሀገርን ሀብት ለግል ጥቅማችን የምናውል ከሆነ ከተጠያቂነት ባለፈ ባለእዳ ነን።

ንጹህና ነውር የሌለበት አገልጋይነት ታማኝነትን ያስቀደመ፣ እውነትና ፍትሕን ያስከተለ ከሁሉ በላይ ደግሞ ለማኅበረሰብ መልፋትን መርህ ያደረገ ነው። በእንዲህ ባለው ብዙኃኑን ባስቀደመ አቃፊ ሥርዓት ስንራመድ ብቻ ነው ሀገር የምንለውጠው። ሀገር የድርጊት ውጤት ናት። የዛሬዋ ኢትዮጵያ በትናንት ድርጊታችን ተፈጥራለች። የነገዋን ኢትዮጵያ በአዲስ መንፈስ እንድትፈጠር ሀገር የቀደመበት፣ ሕዝብ የለጠቀበት እውቀትና ሥርዓት ያስፈልገናል።

አገልጋይነትን ሽራ ሀገሬን ባዶ ያስቀረች ‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል› የምትል አንድ ነውረኛ አባባል አለች። ባለስልጣናትን ከኃላፊነት የምታጎል፣ ከእውነት የምታርቅ ጸያፍ አባባል። እንዲህ ያሉ ከጨዋነትና ከሥነምግባር ያፈነገጡ አባባሎች ሕዝባዊ

> **ጳ**ጉሜን በዚህ ስሜት ስንጀምር አዲሱን ዓመት ሀገር ተኮር በሆነ የአገልጋይነት ንቅናቄ እንድንጀምር፤ ጀምረንም እንድንቀጥል እድል ይሰጠናል

ሳይሆኑ ግለሰባዊ ናቸው። የሆኑ ሆዳም ቡድኖች ሌብነትን ለማበረታታት እና እኔነትን ለማራመድ ሲሉ የሚፈጥሯቸው ናቸው።

እውነተኛ ሹም ሀገር ይጠቅማል፣ ሕዝብ ያገለግላል እንጂ ከድሀ ሀገር ላይ አይሰርቅም። ሀገር ጠቅሞ የተሻረ ባለስልጣን በዓለም ታሪክ የለም። የሚሻሩ፣ የሚገለሉ አገልጋይነትን የማያውቁ ሌቦች ናቸው። ራስን ከመጥቀም አኳያ የሚታዩ አንዳንድ ክፍተቶች ተስተካክለው ሕዝብ ተኮር በሆነ የአገልጋይነት ስሜት ቢተኩ የምንሻትን ኢትዮጵያ ይሰጡናል።

የመንግሥት ተቀዳሚ ተግባር የማኅበረሰቡን ጥያቄ ከመመለስ ጎን ለጎን በበረታ አመራርና ንቃት የአገልግሎቱን ዘርፍ ሕዝብ ተኮር፣ ውጤት ተኮር እንዲሆን መሥራት ነው። እንዲህ ባለው ጠንካራ አሠራር ውስጥ አገልጋይነት አብቦ ሀገር ፍሬ ታፈራለች፤ ሕዝብም ርካታውን በይበልጥ ይገልጻል። ሌቦች ቢኖሩ እንኳን ለሌላው ማስተማሪያ በሚሆን ቅጣት ከስህተቶቻቸው ተምረው ወደአገልጋይነት እንዲመለሱ ይደረጋል።

በአንዲት ‹አገልጋይነት› በምትል ትንሽ ቃል ሁለንተናዊነትን ሥርዓት መግለጽ ይቻላል። በፖለቲካው በማኅበራዊው ያለው እንቅስቃሴ ሁሉ በዚህ ቃል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ጳጉሜን በዚህ ስሜት ስንጀምር አዲሱን ዓመት ሀገር ተኮር በሆነ የአገልጋይነት ንቅናቄ እንድንጀምር፤ ጀምረንም እንድንቀጥል እድል ይሰጠናል።

ከሁሉም ትልቁ ሉዓላዊነት እንኳን ከአገልጋይነት የሚነሳ ነው። ውጤት እና እርካታ ተኮር የሆነው ይሄ እሳቤ ችግሮቻችንን እየቀረፍን በበረታው እንድንቀጥል የጎላ ድርሻ አለው። ብዙኃነት መታወቂያ የሆነች ሀገር ሁሉንም በአንድ ለማስተናገድ ከዚህ የተሻለ ሌላ አማራጭ አያስፈልጋትም።

በማገልገል መገልገል የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያሳይ ነው። ከዚህ ባለፈም የሀገር ፍቅር ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ የመጀመሪያው ነው። ሀገር ማለት ሰው ነው ስንልና ሰው ማለት ሀገር ነው ስንል መገለጫው አገልጋይነት ነው። አገልጋይነት በሌለበት ወይም ባልተካተተበት ወይም ሙሉ ባልሆነበት ሥርዓት ውስጥ የሚመጣ ለውጥ የለም።

የለውጥ ፍልስፍና ከሕዝብ በሕዝብ ለሕዝብ ነው። ይሄ ማለት ሁላችንም ያለንበት፣ ሁላችንም የተሳተፍንበት ማለት ነው። ጋን በጠጠር እንደሚቆም ሀገርም የምትቆመው ዛሬ ላይ እኔ እና እናተ በምናዋጣው ሃሳብ እና ሥነ ምግባር ነው። ይሄ ሁሉ በአንድነት አገልጋይነት ተብሎ ይጠራል። አገልጋይነት መንግሥትና ሕዝብ ያሉበት፣ የእኔ የአንተ የሁላችን ትብብር ነው።

አዲሱን ዓመት ሀገር ተኮር ለማድረግ ሕዝብ የቀደመበት አገልጋይነት ሚናው ላቅ ያለ ነው። ታሪኮቻችንን ለመቀየር፣ ችግሮቻችንን ለመፍታት የትብብር መንፈስ ዋጋው በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በእኔ ውስጥ እናንተ፣ በእናንተ ውስጥ እኔ በሌላው ውስጥም እንዲሁ በስተመጨረሻም የረካችና የበቃች ኢትዮጵያን መውለድ እንችላለን።

ሀገር በማቆም ሂደት ውስጥ የሕዝብ ርካታ ቀዳሚው ነው። ዛፍ በስሩ እንደሚጸና ሁሉ የሀገር ጽናትም በአገልጋይነት በኩል የሚንጸባረቀው የሕዝብ ርካታ ነው። በሥራችን ሕዝብን ማስደሰት በየትኛውም ሙያ ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ኃላፊነት ነው።

በአንድ ሀገር ውስጥ የሕዝብ ይሁንታ የምንም ነገር መነሻ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። አንድን መንግሥት፣ አንድን የመንግሥት ባለስልጣን፣ አንድን ዜጋ ምን ሠራ ብሎ ሊመዝነው የሚችለው የሕዝብ ርካታ ነው።

በጳጉሜን አፋፍ ላይ አሮጌውን ዓመት ወደ ኋላ ጥለን፣ በሐምሌና በነሐሴ ጭጋግ ላይ ተንጠራርተን ወደአዲሱ የብስራት ዓመት አሻቅበናል። ቸር እንድናይ፣ ቸር እንድንሰማ ፤በአገልጋይነት፣ ከኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ...በእኛ ከእኛ ለእኛ በሆነ የአብሮነት መንፈስ ወደአዲሱ ዓመት ጉዞ ጀምረናል።

BETin
BIO & EMERGING TECHNOLOGY INSTITUTE

የኢፌዴሪ መንግስት ለሀገሪቷ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልህቀት ቴክኖሎጂ የሚጫወተውን ሚና በመረዳት፡ ባዮቴክኖሎጂን እንደ አንዱ የምርምር እና ልማት የትኩረት አድርጎ የለየ ሲሆን፤ ይህንን በበላይነት የሚመራ፣ የሚያስተባብር፣ የሚደግፍና የሚቆጣጠር የነበረውን የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን በአስፈፃሚ አካላት ላይ በተደረገው የአደረጃጀት ለውጥ ተከትሎ በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም መሰረት ተቋሙ በአዲስ መልክ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂን ጨምሮ ፤ "የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት" በሚል ስያሜ ተቋቁሟል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት፤ ባዮኢኮኖሚን ለመገንባት፤ እና ለሀገር ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ የባዮቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ የምርምርና ልማት ማካሄድ፤ የማስተባበር፤ የስልጠናና ማማከር ስራዎችን ለመተግበር የሚያስችለውን ተቋማዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል የማሟላት ስራ እያከናወነ ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት የባዮቴክኖሎጂ የምርምር የትኩረት መስኮች 1. የዕጽዋት ባዮቴክኖሎጂ 2. የእንስሳት ባዮቴክኖሎጂ 3. የጤና ባዮቴክኖሎጂ 4. የኢንዱስትሪያል ባዮቴክኖሎጂ 5. የአካባቢ ባዮቴክኖሎጂ 6. ጂኖሚክስና ባዮኢንፎርማቲክስ እንዲሁም በኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ የምርምር የትኩረት መስኮች ስር 1. በምልስ ምህንድስና 2. በናኖቴክሎጂ 3. በማተሪያል ሳይንስና ኢንጂነሪንግ 4. በኮምፒቲሽናል ሳይንስና ኢንተለጀንሲ ሲይስተም ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ወደ ስራ የገባ ሲሆን የምርምር ውጤቶቹን ወደ ማህበረሰብ ለማውረድ የሚረዳውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት አዋቅሮ የተጠናቀቁ የምርምር ውጤቶችን ወደ ተጠቃሚ በማድረስ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በሀገሪቱ በብሔራዊ ደረጃ በዘርፎቹ ላይ ምርምር የሚያደርግ፣ የሚያስተባብር እና ለመሰል ተቋማት ድጋፍ የሚያደርግ ተቋም መሆኑን እየገለጽን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከኢንስቲትዩቱ ጋር በመቀናጀት ለአገር ብልፅግና በጋራ እንድንሰራ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

መልካም አዲስ ዓመት!

የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ፐብሊክ ሰርቪስ
PSETSE

## ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የአገልግሎቱ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ በአማሮ ኮሬ ዞን

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በ2022 ዓ.ም በቅልጥፍናና ተደራሽነቱ፣ በድህነቱና በምቾቱ፣ ተመራጭ እና ትርፋማ የሆነ የትራንስፖርት ድርጅት ሆኖ ማየትን ራዕዩ አድርጎ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡

አገልግሎቱ በአዲስ አበባ እና በልዩ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፐብሊክ ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ለሚሰሩ የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች እንዲሁም ከስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ፣ በበዓላትና ዕረፍት ቀናት ለሌሎች ህብረተሰብ ክፍሎች የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ታሪፍ የሚሰጥ ወጪን በመቀነስ ገቢውን በማሳደግ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶች መስጠት ተልዕኮን ያነገበ ነው፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ከስራ መግቢያና መውጪያ ሰዓት ውጪ የዘመኑ ቴክኖሎጂ በተገጠመላቸው ምቾታቸው አስተማማኝ በሆኑ አውቶቢሶች የህዝብ ትራንስፖርት (ታክሲ) አገልግሎት በመስጠት ለበርካታ ማህበረሰብ ክፍሎች ጊዜና ገንዘብ መቆጠብ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከዚህ ባለፈ በመዲናችን አዲስ አበባ በጥቂት ቦታዎች ብቻ በሚገኘው ዘመናዊ ማሽን በቪዲዮ የታገዘ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ በተመጣጣኝ ክፍያ በመስጠት ላይ ነው፡፡

አገልግሎቱ ከሚሰጠው የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት በተጨማሪ በተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ላይ በመሰማራት በርካታ የማህበረሰብ ችግሮችን ሲፈታና ከህዝቡ ጎን በመሆን መፍትሄ ሲያበጅ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም መካከል



የትምህርት ዘርፉ ተጠቃሽ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትምህርት ቤቶች ግንባታ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ሲሆን ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ ለማድረግ ነባር ትምህርት ቤቶችን ከማደስና ከማስፋፋት ባሻገር ትምህርት ተደራሽ ባልሆነባቸውና የመማሪያ ክፍሎች እጥረት በሚስተዋልባቸው አካባቢዎች አዳዲስ ትምህርት ቤቶችንና ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን የመገንባት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ታዲያ የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎትም ይህንን በጎ ተሞክሮ በመቀላቀል ከዚህ ቀደም በአማሮ ኮሬ ዞን ገንብቶ ለነዋሪው ለማስረከብ ቃል የገባውን ሶስት መማሪያ ክፍሎች ያሉትን ብሎክ ግንባታ በይፋ አስጀምሯል። የአካባቢው ሽማግሌዎች የግንባታው ማስጀመሪያ ዝግጅት ላይ በመገኘት ግበንባታውን በባህላዊ ምርቃት አስጀምረዋል፡፡

በግንባታ ማስጀመሪያ ዝግጅት ላይ የተገኙት የዞኑ ከንቲባ አቶ ትግሉ ዘብዲዮስ እንደተናገሩት፤ "የተማረ ዜጋ ሀገርን ለማሻገር አቅም አለው። በአንጻሩ ደግሞ ያልተማረ ትውልድ ምን ሊፈጥር እንደሚችል ግልጽ ነው። በዞናችን መማር እየፈለጉ መማር ያልቻሉ በርካቶች ‹የትምህርት ያለህ› በማለት ላይ ናቸው። ይህን የተረዳው ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ ዞናችን ድረስ መጥቶ መማሪያ ክፍሎችን ሰርቶ ለማስረከብ ግንባታውን በማስጀመሩ ትምህርት በተጠሙ ህጻናትና በዞኑ ስም ምስጋናዬን ለመግለጽ እወዳለሁ" ብለዋል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን በመወከል በግንባታ ማስጀመሪያ ዝግጅቱ ላይ የተገኙት አቶ ሽፈራው አባቡ እንደገለፁት፤ በዋና ዳይሬክተሯ በወይዘሮ ፍሬህይወት ትልቁ በተሰጠ መመሪያ መሰረት የመማሪያ ክፍሎቹ ግንባታ ሌት ከቀን በርትቶ በመስራት ተጠናቀው ለ2016 የትምህርት ዘመን በመማሪያ ክፍሎች እጥረት ምክንያት ቤት የዋሉና ትምህርት የተጠሙ የዞኑ ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ እንዲሁም ትምህርት ያልጀመሩ ህፃናትም ትምህርት እንዲጀምሩ፤ ቃላችንን ጠብቀን የመማሪያ ክፍሎቹን ግንባታ በወቅቱ በማጠናቀቅ እናስረክባለን ብለዋል፡፡

በዞኑ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ሊገነቡ መሆኑን ሰምተው የተሰበሰቡ የአካባቢው ህፃናት ወደፊት ተምረው ዶክተር፣ ፓይለትና መምህር መሆን እንደሚፈልጉ በልጅነት ጣፋጭ አንደበታቸው ለልዑካን ቡድኑ ከምስጋና ጋር አስረድተዋል፡፡ መማር እንፈልጋለን ሲሉም ለመማር ያላቸውን ብርቱ ፍላጎት ተናግረዋል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ከእረኝነት እስከ ሕክምና ፕሮፌሰርነት

**ክብረአብ በላቸው**

ምሁር ለሚለው ቃል አቻ እንግሊዝኛ ትርጉሙ ኢንተሌክቹዋል የሚለው ፍቺ ነው። የአማርኛ ቋንቋ ደግሞ ምሁር የሚለውን ቃል ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው ብሎ ይተነትነዋል ወይም ትርጉም ይሰጠዋል። በትምህርት የሚገኘው ዕውቀት በተግባር ለውጥና መሻሻል ካላመጣ ትምህርት መማሩና ማስተማሩ በራሱ ትርጉም የለውም ይላሉ ብዙዎች። የአንድ ሰው በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ፋይዳ የሚኖረው በራስና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ሲያስችል ብቻ ነው።

የምሁር ዕውቀት የሰዎችን ኑሮና አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ። በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት በማሻሻል ላይ ማዕከል ያደረገ መሆንም ይኖርበታል። ስለዚህ፣ አንድ ሰው በትክክል “ምሁር” ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው። ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

ሆኖም ሁል ጊዜ ትልቁ የመከራከሪያ ነጥብ ብያኔውን በተመለከተ በግልፅ ማስቀመጥ አለመቻል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አረዳድ ምሁር ማለት በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አልፎ ዲግሪ የያዘ ሰው ማለት ነው።


ምሁር ምን ማለት እንደሆነ ግን በምሳሌ በቀላሉ እንረዳለን። ሻማ ብንወስድና ሻማ በካርቶን ውስጥ እንዳለ በቤት ውስጥ ቢቀመጥ እንደማንኛውም በቤት ውስጥ እንዳለ ዕቃ ነው። የበራ ሻማ ግን ክስተት ነው። ሻማውን ከብርሃኑ ለይተህ አታየውም። የበራው ሻማ ለራሱ ሲል አይበራም ለሁላችን እንጂ፤ ምሁር ማለት የበራ ሻማ ማለት ነው። የተማረ ማለት ደግሞ ያልበራ ሻማ ማለት ነው፤ የመብራት አቅም አለው ነገር ግን አልበራም።

ስለዚህ ምሁር ማለት በልምድ፣ በትምህርትና በልዩ ልዩ መንገድ ያገኛቸውን ማስተዋሎችና ዕውቀት በሐሳብ መልክ ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ሰው ነው።

ለዚህ ቃል ብቁ ሆነው የተገኙ ጥቂት የሚባል ቁጥር የሌላቸው በዓለም መድረክ ላይ አዳዲስና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግኝቶችንና ፈጠራዎችን ይዞ ብቅ በማለት የበርካቶችን አንገብጋቢ ችግር የፈቱና ብዙዎችን በስራዎቻቸው ያስገረሙ በርካታ ኢትዮጵያውያን አሉ። ከእነዚህም ሰዎች ውስጥ የላፓራስኮፒክ ህክምና ፕሮፌሰር ምትኩ በላቸው አንዱ ናቸው።

ታዋቂው የቀዶ ህክምና እስፔሻሊስት ፕሮፌሰር ምትኩ በላቸው የተወለዱት በምዕራብ ሸዋ ወንጪ ሲሆን እድሜያቸው 12 ዓመት ሲሞላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ፕ/ር ምትኩ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከነበረበት የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውጪ የትምህርት እድል አግኝተው ወደ ቤልጂየም በማቅናት የህክምና ትምህርታቸውን ተከታትለው በዓለማችን አንቱ ከተባሉ የቀዶ ህክምና ስፔሻሊስቶች ተርታ መሰለፍ ችለዋል።

ፕሮፌሰር ምትኩ እስከ አስራሁለት ዓመታቸው ድረስ ወደ ትምህርት ገበታ ሳይቀላቀሉ በእረኝነት አሳልፈዋል። ይህም የሆነው በትውልድ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት ባለመኖሩ ነው። የቀለም ትምህርታቸውን አንድ ብለው የጀመሩት በጅማ ከተማ ነበር። በኋላም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመድሃኒዓለም ትምህርት ቤት መከታተል ችለዋል። ከሌሎች የዕድሜ ዕኩዮቻቸው ዘግይተው ማለትም በአስራ ሁለት ዓመታቸው ስለነበር የቀለም ትምህርት የጀመሩት ይህንን ማካካስ ስለነበረባቸው እና የትምህርት አቀባበላቸው ከፍ ያለ በመሆኑ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሰባት ዓመት በማጠናቀቅ በ19ኝ ዓመታቸው የሕክምና ትምህርት ለመከታተል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ተቀላቅለዋል።



**ፕሮፌሰር ምትኩ በላቸው**

የሕክምና ትምህርት ለመከታተል ምክንያት የሆነቻቸው የታላቅ ወንድማቸው ሞት እንደሆነ ፕሮፌሰር ምትኩ ይገልፃሉ። ህመም ሳይታይበት በድንገት የመሞቱ ምክንያት ምንድነው በማለት ለመመራመር እንደተነሱና አንድ ቀን የዚህን ምክንያት ባውቅ በሚል ጉጉት ሕክምና ለመማር እንዳለሙ በአንድ ወቅት ተናግረዋል።

በወቅቱ አንድ ለእናቱ የነበረውን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መቀላቀል ቢችሉም በስድስት ኪሎ የህክምና ትምህርት ስላልነበር ለህክምና ቅርበት ወዳለውና አራት ኪሎ ወደሚገኘው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በመግባት ትምህርታቸውን ለአንድ ዓመት ከተከታተሉ በኋላ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚሰጥ የስኮላርሺፕ ፈተና በብቃት በማለፍ ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ የመማር እድል አግኝተዋል። በዩናይትድ ኪንግደም ወይም በአሜሪካ የሕክምና ትምህርት ለመከታተል እቅድ የነበራቸው ፕሮፌሰር ምትኩ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ የቤልጂየም መንግስት በሀገረ ቤልጅየም ትምህርት እንዲከታተሉ እድል ሰጣቸው። ከጓደኞችና በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች በቤልጅየም የቋንቋ ችግር ቆይታህን አስቸጋሪ ስለሚያደርገው በቅድሚያ ቋንቋ ተማር የሚል ምክር ስለቸሯቸው ወደ ቤልጅየም በመሄድ ፈረንሳይኛ በመማር ከዚያም የሕክምና ትምህርት በመከታተል በመጨረሻ የላፕራስኮፒክ ቀዶ ጥገና ባለሙያ እና ፕሮፌሰር መሆን ችለዋል።

የተሻሻለውን አፒታይት የሚገድብ በጨጓራ ላይ የሚታሰር የሚጠብ እና የሚሰፋ ቀለበት ወይም በእንግሊዝኛ Laparoscopic adjustable Silicone gastric banding የፈጠሩት ፕሮፌሰር ምትኩ ስለዚህ የፈጠራ ሥራቸው ሲናገሩ፤ ብዙ ደም ሳይፈስና ህመም ሳይኖር የሚሰጥ የሕክምና አይነት መሆኑን አስረድተዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት በትንሽ ቀዳዳ በመጠቀም የማይክሮ ካሜራ ወደ ውስጥ በማስገባት በጣም ትናንሽ በሆኑ መሳሪያዎች የሚከናወን የሕክምና አይነት በመሆኑ ከአንድ ሴንቲሜትር ባልበለጠ የሰውነት ቀዳዳ የሚከናወን ሕክምና በመሆኑ ሰዎች ከሰመመን ሲነቁ የሕመም ስሜታቸውን በእጅጉ የቀነሰ ያደርገዋል ይላሉ። ይህም የሕክምና ቴክኖሎጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕክምና ሳይንስ ትልቅ አብዮት ያመጣ የፈጠራ ሥራ እንደሆነም በአንድ ወቅት ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በጥቁር አንበሳ የቀዶ ጥገና ወርክሾፖችን ጨምሮ በብዙ ቦታዎች ያስተማሩት ላፓሮስኮፒክ ቀዶ ጥገና ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር ተማሪዎች ዕውቀት አስጨብጠዋል። ብዙ ቦታዎች በመጓዝ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ብዙ የቀዶ ህክምና ዘመቻዎችን እና ተልዕኮዎችን ከ10 እስከ 15 ሰዎች በማዘጋጀት በመላ ኢትዮጵያ ቀዶ ጥገና ማካሄድ እና ስልጠናዎችን ለመስጠት አዘውትረው ሰርተዋል። በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ እና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የቀዶ ጥገናውን ዲፓርትመንት በማቋቋም ለ3 ዓመታት ስልጠናዎችን በመስጠት ተማሪዎች ለማብቃት ጥረዋል።

የልጅነት ቤታቸው ለሆነው ወንጪ ብዙ ነገሮችን ማበርከት የቻሉት ፕሮፌሰሩ በልጅነታቸው ሁሉም ሰው እሳቸው ያገኙትን እድል እንዲያገኝ ትምህርት ቤት የመገንባት ህልም ስለነበራቸው ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎችና አጋር አካላት ጋር በመተባበር በጎ አድራጎት ድርጅት መስርተው በወንጪ ሐይቅ ዙሪያ ትምህርት ቤት መገንባት ችለዋል። በትምህርት ቤቱ ዛሬ ከ1000 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ። በርካቶችም ትምህርታቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀው ከሕክምና እስከ ምሕንድስና እና ህግ ባሉ ዘርፎች ኅበዝ ሆነው ሀገራቸው እያገለገሉ ይገኛሉ።

በአካዳሚክ የላቀ ውጤት ያላመጡ ወጣቶችን እንደ ሽመና ባሉ ዘርፎች በማሰልጠን ወደሥራ ያስገቡት ፕሮፌሰር ምትኩ፣ ወጣቶች ሲሳካላቸው በማየታቸው ኩራት እና ደስታ እንደሚሰማቸው ተናግረው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በትውልድ አካባቢያቸው ወንጪ በሕክምና መሳሪያዎች የተሟላ እና አምቡላንስ ያለው ክሊኒክ በመገንባት የአካባቢ ሕብረተሰብ በአቅራቢያው የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሰርተዋል።

ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት መጨመር Obesity በሰውነታችን አላስፈላጊና ከፍተኛ መጠን ያለው triglyceride ተብሎ የሚጠራው ስብ (fat) በሆድ፣ በመቀመጫ፣ በላይኛው የእጅ ክፍል፣ በትከሻና በሌሎች የሰውነታችን ክፍል በመከማቸቱ ምክንያት የሚፈጠር የጤና ችግር ነው።

ፕሮፈሰር ምትኩ በላቸው፣ ከመጠን በላይ ውፍረት ሳቢያ የሚከሰት የጤና ችግሮችን ለመቀነስ የሚረዳ የሕክምና ዘዴ ፈጥረው፣ ለበርካቶች የጤና፣ የደስታ የእፎይታ ምንጭ ሆነው፣ በሕክምናው ዓለም ስማቸውን እና የሀገራቸውን ስም ከፍ አድርገው አስጠርተው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለወገናቸው ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ ከፍተው፣ አስተምረው በርካታ በጎ አድራጎት ስራ ሰርተው፣ ከጉዟቸው፤ ከጥንካሬያቸው፤ ከድካማቸው እንድንማር ታሪክን እንድናውቅ ዓለም ስለ መሰረታቸው ስለሀገራቸው ታሪክ፣ ባህል፣ እንዲያነብ፣ ታሪካቸውን በመጽሐፍ ጽፈው እሳቸው እንደሚሉት የሕይወት ተራራን ወጥተው ጉዟቸውን አገባደው ነው ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት።

ከገጠሪቷ ወንጪ የእረኝነት ሕይወት እስከ ሌዥ (ቤልጅዮም) በዘለቀው ስኬት ከባዶ እግር ተነስተው ታዋቂ የቀዶ ጥገና ሀኪምነት አለፍ ሲልም እስከ ሕክምና ሊቅነት የደረሱት እኚህ ጉምቱ ኢትዮጵያዊ ምሁር ፕሮፌሰር ምትኩ በላቸው የአውሮፓ ጋዜጦች Lord of the Ring በሚል ቅፅል ይጠሯቸው ነበር። ለዚህ ምክንያት የሆናቸው ፕሮፌሰሩ የፈበረኩት የፈጠራ ውጤት ነበር።

በውጤቱም አውስትራሊያ፣ አውሮፓ፣ ሞሮኮ፣ ቤኒን፣ ሴኔጋል፣ ቶጎ እና ኮንጎን ጨምሮ ለሕክምና ኮንፈረንስ እና ለማስተማር እና ቀዶ ጥገና ለማድረግ በዓለም ዙሪያ ተመላልሰዋል። በሕክምናው ዘርፍ የፈጠራ ሥራውን ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ያደረጉበትን አጋጣሚ በአንድ ወቅት ሲናገሩ፤ ‘’ከሁለት አሥርተ ዓመታት በፊት በምሠራበት ጊዜ፣ ቤልጂየም በባቫሪያ ሲቪል ሆስፒታል፣ ክብደቷን ለመቀነስ የረዳኋት በከባድ ውፍረት የምትሠቃይ ነርስ ነበረች። በወቅቱ ከመጠን ላለፈ ውፍረት ሕክምና የቀዶ ጥገና መፍትሔ በሰው ልጆች ላይ ገና አልተሞከረም ነበር፤ ውስብስብ ሂደቶችም ያሉት ነበር። ነገር ግን ሌት ተቀን ካጠናሁ በኋላ ለነርሷ የተሳካ ቀዶ ጥገና ማድረግ ቻልኩ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ከመጠን ያለፈ ውፍረት ቀዶ ጥገና ስፔሻሊስት ሆንኩ’’ ይላሉ።

በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉ ለሳይንሱ ዓለም አዲስ ነገር የፈጠሩ ግሩም ሳይንቲስት ነበሩ። በህይወት ዘመናቸው 40,000 ቀዶ ጥገናዎችን አድርገዋል። 30ሺ የሚሆኑት በውጪ ሀገራት 10ሺ የሚሆኑትን ኢትዮጵያ ውስጥ አድርገዋል። ከቀዶ ጥገና ስራ ጡረታ ከወጡ በኋላ ህይወታቸው እስከለፈበት ወቅት ድረስ በኢትዮጵያ በተለያዩ ሆስፒታሎች ማለትም በጥቁር አንበሳ፣ በቤቴል እና በቅዱስ ያሬድ የሠሩ ሲሆን እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ እውቀትና እና ልምዳቸውን ለቀጣዩ ትውልድ እያካፈሉ ቆይተዋል።

የኪሊማንጃሮን ተራራን በ67 ዓመታቸው የወጡ ጠንካራ ሰው፣ ጉምቱ ምሁር በኢትዮጵያና በመላው ዓለም በሕክምናው ዘርፍ ላይ ሰፊ ጥናት እና ምርምር በማድረግ የሚታወቁት ፕሮፌሰር ምትኩ በላቸው በሚኖሩበት ቤልጂየም ሊየዥ ከተማ ባደረባቸው ድንገተኛ ህመም በተወለዱ በ79 ዓመታቸው ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት። እኛም ለእኚህ የሀገር ዋርካ እና ባለውለታ ነፍስ ይማር እንላለን።

# ስፖርት





## ‹‹ባለኝ ልምድና አቅም ስፖርቱን በማገልገሌ ደስተኛ ነኝ››

**- ደራርቱ ቱሉ**

ብርሃን ፈይሳ

የዘመናዊው ኦሊምፒክ መስራች ፒር ደ ኩበርቲን ስፖርትን የሚገልጹት «... ለእኔ የሃይማኖቴን ያህል ስሜት ይሰጠኛል» ሲሉ ነው፡፡ በእርግጥም የስፖርት ፍቅር በቀላሉ ከውስጥ የማይወጣ በደም ስር ሲዘዋወር የሚኖር ነው፡፡ በርካቶች ከልጅነታቸው የተጠናወታቸው የስፖርት ፍቅር ተወዳዳሪነታቸውን አቁመው እንኳን ሊርቁት አይቻላቸውም፡፡ ይልቁንም እንደማግኔት እየሳበ እንዲያገለግሉት ያደርጋል፤ ምክንያቱም የሚገኘው የመንፈስ እርካታ በዚያው ልክ በመሆኑ ነው፡፡

ከተወዳዳሪነት ዓለም የራቁ ስፖርተኞች በአሰልጣኝነት፣ በቴክኒክ አማካሪነት፣ በተንታኝነት፣ በቡድን መሪነት፣ በስራ አስፈጻሚነት፣... መሰማራታቸው የተለመደ ነው፡፡ ይህ ስፖርትን ከሌሎች ዘርፎች ልዩ የሚያደርገው ሲሆን፤ ሊተውት የማይቻል ሱስ ነው፡፡ በኢትዮጵያም በተመሳሳይ ስፖርተኞች ተወዳዳሪነትን ካቆሙ በኋላ በተለያዩ ስፖርታዊ ጉዳዮች ከማገልገል ወደኋላ አይሉም፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው አትሌቲክስ ሲሆን፤ እጅግ በርካታ አንጋፋና ሩጫን ያቆሙ አትሌቶች የወከሉትን ሃገር ዳግም በአማተርነት እያገለገሉት ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያአትሌቲክስፌዴሬሽንንበፕሬዚዳንትነት እየመራች የምትገኘው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ደግሞ የአገልጋይነት ተምሳሌት ናት፡፡ ከባርሴሎና እስከ አቴንስ በድል ህዝቧን ያስፈነደቀችና ለሠንደቅዓላማዋም



ያነባችው እንቁ አትሌት ከሩጫ ሕይወቷ ከተለየች በኋላ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንትነት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን መቀላቀሏ የሚታወስ ነው፡፡ እስካሁንም በመምራትና ዝናን ያተረፈችበትን ስፖርት እንዲሁም በስፖርቱ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ሁሉ በማገልገል ላይ ትገኛለች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ‹‹ቀድሞ በሩጫው ሃገሬን ሳገለግል ቆይቼ ራሴን ልለውጥ ችያለሁ፤ ከውድድር ከተሰናበትኩ በኋላ ደግሞ ባለኝ ልምድና አቅም ስፖርቱን ለማገልገል በመብቃቴ ደስተኛ ነኝ›› ትላለች፡፡

ወደ ፌዴሬሽኑ በአመራርነት የተመለሰችበትን ሁኔታም ስታስታውስ ‹‹እንደሚታወቀው በሩጫ ሕይወት አትሌቶች በጉዳት፣ ስፖርት በቃኝ በማለት፣ በወሊድ፣ ከሃገር በመውጣት፣... ከስፖርቱ ይርቃሉ፡፡ እኔም ከውድድር ዓለም ስወጣ ከስፖርቱም ርቄ ነበር የቆየሁት፤ ይሁንና ጓደኞቼ እነ ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም፣ ገዛኸኝ አበራ፣ ስለሺ ስህን፣ ማርቆስ ገነቴ፣... አትሌቲክሱን ለመምራት መምጣታቸውን ተከትሎ ዘግየት ብዬ ተቀላቅያቸዋለሁ፡፡ ጥሪ ያደረገልኝ ደግሞ ቀድሞ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት የነበረው ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ ነው›› በማለት ተናግራለች፡፡

በዓለም ላይ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው የስፖርት ፌዴሬሽኖች ቀዳሚው የዓለም አትሌቲክስ ሲሆን በኢትዮጵያም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መሆኑን የጠቀሰችው ደራርቱ፣ በበርካታ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች ተሳታፊና ውጤታማ የሆነውን ፌዴሬሽን ማገልገል ትልቅ ክብር እንደሆነም ታብራራለች፡፡ ፌዴሬሽኑን በአመራርነት ተቀላቅላ በዓመታት ያካበተችውን ልምድ ሃገርን ወደ መጥቀም እንድትለውጥ ያደረጓትን አትሌቶችንና ከሯጭነት ዘመኗ እስከ አሁን ድረስ እያከበረ ለዚህ ያደረሳትን ህዝብም አመስግናለች፡፡

በአንጻሩ እንደ እሷ በሙያቸው በዙ ማበርከት እየቻሉ ከፌዴሬሽኑ የራቁ አትሌቶችን ወደ ፌዴሬሽኑ ተመልሰው የአቅማቸውን እንዲያበረክቱና ለተተኪዎችም ሞራል እንዲሆኑ ጥሪዋን አቅርባለች። ደራርቱ አብዛኛዎቹ አትሌቶች ከስፖርቱ ሲሰናበቱ ሙሉ ለሙሉ ከፌዴሬሽኑ የሚርቁበትን ምክንያት «ምናልባትም የስራ ድርሻ አይኖረን ይሆናል» በሚል እንደሚሆንም ጠቁማለች፡፡ ነገር ግን በስፖርት ሕይወት የቀድሞ አንጋፋ አትሌቶች አሁን ካሉት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት በርካታ ምክር በማግኘት ትልቅ ደረጃ ይደርሳሉና እገዛቸውን ቢያደርጉ ትመክራለች፡፡

ምንም እንኳን በስፖርቱ በአሰልጣኝነት አሊያም በሌሎች ኃላፊነቶች ላይ ገብተው ባይሳተፉም በውድድር ላይ ካሉ አትሌቶች ጎን በመቆምና ሞራል በመስጠት ማገልገል እንዳለባቸውም ጠቁማለች፡፡ ስፖርቱ ያሳወቃቸው ስኬትንም የተቀዳጁበት ነውና በየትኛውም የአትሌቲክስ ዘርፍ ሃገራቸውን በድጋሚ ሊያገለግሉ እንደሚገባም አሳስባለች፡፡

ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ ከአትሌትነት እስከ ብሄራዊ ፌዴሬሽን አመራርነት እንዲሁም የአህጉር አቀፉ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን የቦርድ አባል ከመሆኗ ባሻገር በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የአትሌቲክስ ማህበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን እያገለገለችም ትገኛለች፡፡ በዚህ ከሃገር እስከ አህጉር በተሻገረ አስተዋጽኦም ለበርካቶች ተምሳሌት ሆናለች፡፡ በዚህም የዓለም አትሌቲክስ ለረጅም ጊዜ ስፖርቱን በማገልገል ከሳምንት በፊት በቡዳፔስት ዓመታዊው ታላቅ የሽልማት ስነስርዓቱ ላይ የዕድሜ ልክ ሽልማት እንዳበረከተላት ይታወሳል፡፡ ይህ ሽልማት በስፖርቱ የተለየ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የስፖርቱ ሰዎች የሚሰጥ ሲሆን፤ የዘንድሮውን ጨምሮ ሶስት ጊዜ በመሸለም በኢትዮጵያ ክብሩን ካገኙ ጥቂት ግለሰቦች መካከል አንዷ ከሴቶች ደግሞ ብቸኛዋ ናት፡፡


የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

**የጨረታ ማስታወቂያ**
**የጨረታ ቁጥር EEU-PPM/01/2016(NCB)**

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ጽ/ቤት 4,300 (አራት ሺ ሶስት መቶ) ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ህንፃ ከህንፃ ባለቤቶች በጨረታ አወዳድሮ መከራየት ይፈልጋል። ስለሆነም ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ድርጅቶች በጨረታ መወዳደር ይችላሉ።

1. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ የሚያቀርቡና በመስኩ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
2. የጨረታ ሰነዱን ከጳጉሜ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል የኢ.ኤ.አ. ፕሮጀክቶች ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ጽ/ቤት ከካቴድራል መብራት ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ በተለምዶ እሪ በከንቱ በሚባለው አካባቢ በርጌስ ክሊኒክ ህንጻ ላይ 5ኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ።
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም የዋስትና ጊዜው ከሚያበቃበት ቀን በኃላ 28 ቀን ተጨማሪ ጊዜ ያለውን የባንክ ዋስትና (Bank Guarantee) በኢ.ኤ.አ. ፕሮጀክት ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ወይም EEU-PMM ስም ተዘጋጅቶ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በሰንጠረዥ በተገለጸው ብር መጠን ማቅረብ አለባቸው።
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ጨረታ ቁጥር EEU-PPM/01/2016 (NCB) የሚል ምልክት በማድረግ እስከ መስከረም 9 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ በኢ.ኤ.አ. ፕሮጀክቶች ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ጽ/ቤት ከካቴድራል መብራት ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ በተለምዶ እሪ በከንቱ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በርጌስ ክሊኒክ ህንጻ ላይ 3ኛ ፎቅ በመቅረብ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት /ባይገኙም/ መስከረም 9 ቀን 2016 ከቀኑ 8፡30 ሰዓት ላይ ይከፈታል።
6. ስለጨረታው ዝርዝር መረጃ የጨረታ ሰነዱን ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ ጠዋት 2፡00 6፡00 እና ከሰአት በኋላ 7፡00 11፡00 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ 2፡00-6፡00 ሰዓት ይመልከቱ ።
7. የፕሮጀክቶች ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
8. ተጫራቾች መረጃ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 0111263159 /011-127-55-03 መደወል ይችላሉ።

**በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**
**የፕሮጀክቶች ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ጽ/ቤት**



## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ታምሩ ቶሎሳ የሰሌዳ ቁጥር 01-67255 የተሽከርካሪው ዓይነት ባለሦስት እግር ባጃጅ ከላይ የተጠቀሰው ባለንብረት በቀን 25/12/2015 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የተሽከርካሪው ሰሌዳ የጠፋባቸውና ምትክ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል። በመሆኑም ይህንን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የመነ አቢቹ ክ/ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

ንብረትነቱ የአቶ ምህረቱ ደስታ የተሽከርካሪው ዓይነት ባለ 3 እግር ባጃጅ ታክሲ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-32777 ደህ የፊት ሰሌዳ የጠፋ ስለመሆኑ በቁጥር 1709/6ወፖ/15 በቀን 01/12/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተገልጾልናል። ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ፣ በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እናሳውቃለን።

**የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስሥት የሀዲያ ዞን**
**መንገዶችና ትራንስፖርት መምሪያ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ሚፍታህ በያን ጀማል የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B50124 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር AZR600415575 ሞዴል CBA-AZR60G-AREEHP የሞተር ቁጥር 1AZ-5142672 የሊብሬ ቁጥር 438135 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ29/12/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለስልጣን የኮልፌ ቀራኒዮ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ/በአመልካች/በፍ/ባለመብት አቶ ዳውድ ይመር አልዩ እና በተከሳሾች/በተጠሪዎች/በፍ/ባለዕዳዎች እነ ሙሃመድ ይማም መካከል ስላለው የውርስ ክስ ጉዳይ በተከሳሾች/በተጠሪዎች/በፍባለዕዳዎች 1ኛ ሙሃመድ ይማም፣ 2ኛ አሲያ አህመድ፣ 3ኛ መካ ሙሄ በ08/02/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ8፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 2ኛ ውርስ ችሎት እንዲቀርቡ እንገልጻለን።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**